# ምዕራፍ ሠላሳ አራት

## የዐርቀ ጥምጥምታ ፡ ቴዎድሮስና ናፒዩር የተለዋወጡት መልእክት

ቀድሞውኑ የመነመነው ያፄ ቴዎድሮስ ጦር ፣ አሁን ከፊታውራሪ ገብርዬ ሞት ወዲህ እጅግ ተዳከሟል ማለት ይቻላል ። ከገብርዬ ሞት በፊት ወታደሩ ወደ መቅደላ ምሽግ ተሰብስቦ እንዲገባ በታዘዘ ጊዜ ፣ ግማሹ ትእዛዛቸውን አክብሮ ሲገባ ግማሹ ባንድ ወገን የንጉሡን መዳከም በመረዳት ፣ በሌላም ወገን ጦርነት በመሰልቸት ፣ «መቅደላ ገብተን በፈረንጅ እሳት አንቃጠልም» ብሎ ወደ አገሩ ጉዞ መዠመሩ ይታወሳል ።(1)

ፊታውራሪ ገብርዬ ፣ በእንግሊዝ ጦር መካከል ገብተው እየተዋጉ የሞቱት ሚያዝያ 3 ቀን ዐርብ የስቅለት ለት ነው ። በዚሁ ዕለት ማታና በማግሥቱ በየሠፈሩ ሁሉ ፣ በሕይወት ያለው በጦርነቱ ላይ ለሞተው ዘመድ እያለቀሰ በየሠፈሩ ዋይታና ለቅሶ በርክቶ ነበር ። የዚህንም ሁኔታ የዘመኑ ጸሐፊ ሲያወሱ ፣ በነገታው ቅዳሜ ሹር (ስዑር) ለት ፣ ንጉሡ ከአፋፍ ሆነው ቁልቁል በመነጥር ይመለከቱ እንደ ነበረና እንግሊዞችም ወድቆ ያደረውን ቁስለኛ እያስነሡና ወደ ሠፈራቸው እየወሰዱ የሞተውንም ይቀብሩ እንደ ነበረ ካመለከቱ በኋላ ፣ አከታትለው ከእንግሊዞች ዘንድ « . . . የእንግሊዝ ንግሥት ስለ ፍቅር (ስለ ወዳጅነት) ወደርስዎ (መልክተኞች) ቢሰዱዋቸው አሰሩዋቸው 1 መልሰው በልመና ይፍቱልኝ ብለው ቢለምኑ አልፈታም አሉ ። አሁንም ተልከን መጥተን ምን አመጣችሁ ብለው ሳይጠይቁን በጠብ ተቀበሉን ። አሁን ያለፈው ዐለፈ አንድ ጊዜ . . . ሁለተኛ የክርስቲያን ደም አይፍሰስ ። ሰዎቻችንን ይስጡን ፣ እስሮችም ያልታሰሩትም በሐበሻ የተወለዱት (ክልሶች) ሳይቀር የነጭ

1 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ያለቃ ወልደ ማርያም ጽሑፍ ገጽ 53—54

ዘር የሆነ ይስጡን ። ከርስዎ ጋርም እንገናኝና ከንግሥታችን ያመጣነውን ቃል እንናገራለን ። ከዚህ ቀደም በደል ከርስዎ ነው እንጂ ፣ ከእኛ በደል የለም» ብለው እንግሊዞች ላኩ የሚል መልእክት መምጣቱን ካመለከቱ በኋላ ፣ በዚሁ ንዴት ንጉሡ ራሳቸውን በሽጉጥ ለመግደል እንደ ሞከሩና ወገኖቻቸው ከእጃቸው ለማስለቀቅ ሲተናነቁ ወደ ሽቅብ መተኰሱን ይገልጻሉ ።[1]

ኢትዮጵያዊው ጸሐፊ ፣ ከእሮጌ ጦርነት በኋላ ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው ፣ መልክተኞች ወዳፄ ቴዎድሮስ በቅድሚያ የላኩ እንግሊዞች መሆኑን ሲያመለክቱ በእንግሊዞቹ በኩል ግን ፣ የመልእክቱ አላላክ የመነጨው ካፄ ቴዎድሮስ በኩል ነው የሚል ተመዝግቧል ። ምናልባት የቃል መልእክቱ ከእንግሊዞቹ ወገን ከመጣ በኋላ ፣ የመጀመሪያው በጽሑፍ የሆነው መልእክትና የዕርቁ ፍለጋ ካፄ ቴዎድሮስ ዘንድ ተልኮ ይሆናል ።

በእርግጥም ከእሮጌው ጦርነትና ከፊታውራሪ ገብርዬ ሞት በኋላ ፣ ዐርብ ለቅዳሜ ስዑር አጥቢያ እርሳቸውም ስለ ገብርዬ ሞት ፣ የቀረውም ለየዘመዱ ሲያለቅስ በእስረኞቹም ዘንድ ወሬው ተሰምቶ ፣ 'እንግዲህ እኛንም ይፈጁናል' የሚል ሥጋት ውጪ ቸው ሳለ ፣ በመካከሉ በዐፄ ቴዎድሮስ ትእዛዝ ቀደም ብለው ፍላድና ወልድሜየር ከምስተር ራሳም ጋር እንዲመካከሩና አሳብ እንዲያቀርቡ ፣ «እስቲ ምን ማድረግ እንደሚሻል አሳባችሁን ግለጡልኝ» ቢሉ ፣ ወልድሜየር «የሚሻለው የሰላሙ መንገድ ብቻ ነው» አለ ። «አንተስ ፍላድ ምን ይሻላል ትላለህ?» ቢሉዋቸው ፣ «ምስተር ራሳም ያሉትን መፈጸም የሚገባ ይመስለኛል» አሉ ። ከእሮጌው ውጊያ በፊት ራሳም ያለው ፣ «እኔም ተልኬ የመጣሁት እስረኞቼን አስፈትቼ በርስዎና በእንግሊዝ ንግሥት መካከል መልካም የወዳጅነት ግንኙነት ለመፍጠር ነበር ። አሁንም የመጣው የእንግሊዝ ጦር እስረኞቹን ከማስፈታት በቀር ሌላ ዓላማ የለውም» ብሏቸው ነበር ።[2]

የእሮጌው ጦርነት ከተደረገ በኋላ ፣ ወደ እንግሊዞች መልዕክት ይዞ ለመሔድ አንደኛ ከምስተር ራሳም ጋር ከእንግሊዝ

---

1 ቍዘላ..........ገጽ 44—45

2 Journal Royal Sintice Society..........The last two letters of Emperor Theodore..........B. Appteyerd and R. Pankhurst P. 27



መንግሥት ተልኮ መጥቶ የነበረው የመቶ አለቃ ፕሪዶ ፣ ሁለተኛ እዚሁ ጐንደር ብዙ ዘመን በወንጌል መልእክተኝነት መጥተው በመቀመጥ ካፄ ቴዎድሮስ የሚተዋወቁትና አማርኛም የሚያውቁት ምስተር ማርቲን ፍላድ የሚባሉት የጀርመን ተወላጅ ተመረጡ ። ፕሪዶ ከሕንድ አመጣጡንና ፍላድም ከዚህ በፊት ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው እንደ ነበረ አንባቢ ያስታውሰዋል ። ከነዚህም ጋር ከዐፄ ቴዎድሮስ ወገን አማቻቸው ደጃች ዓለሜ አብረው እንዲሔዱና ደብዳቤውን እንዲያስረክቡ ተመረጡ ። የደብዳቤው ቃል ቀጥሎ ያለው ነው ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፣ አሐዱ አምላክ በሦስትነቱ ፣ ባንድነቱ በክርስቶስ ያመነው ካሣ ፣ መቼም ያገሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁላችሁ ሽሽታችሁን አትተዉም ። ክርስቲያኑን ሁሉ ጉልበት አለኝ መስሎኝ ካረመኔ አገር አግብቸው ። ወንድ የሌላት ቆንጆ አለች ፤ ወንድ የነበራትም ቆንጆ ነበረች ፣ ትላንትናም የሞተባት ትኖራለች ። ሽማግሌ ልጅ የሌለው ፣ ባልቴት ልጅ የሌላት ፣ እኔ የምጠውራቸው ብዙ በከተማየ አሉ ። እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ፍቀዱአቸው ። ያረመኔ አገር ነውና ። ያገሬ ሰው ገብር ሥራት ግባ ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ ። እናንተ ግን ፣ በስራት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ ። እኔን ወደውኝ የተከተሉኝ ሰዎች አንድ እርሳስ ፈርተው ጥለውኝ ሸሹ ። ብትቃጡአቸው ከሮጡ ሰዎች ጋር አልነበርሁም ። ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውየ ነው ። ያገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዞአል ፣ እስልሞአል እያለ ዐሥሩን ምክንያት ይሰጠኝ ነበረ ። እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም ይስጠው ፣ እንደ ወደደ ይሁን ። እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ሁሉን ልገዛ አሳብ ነበረኝ ። እግዚአብሔር ቢነሣኝ ልሞት ፤ አሳቤ ይህ ነበረ ። ከተወለድሁኝ እስታሁን ወንድ እጇን ጨብጦት አያውቅም ነበረ ። ሰዎች ሲሸሹ ተነሥቼ ማረጋጋት ልማድ ነበረኝ ፣ ጨለማ ከለከለኝ ። ትላንትና በደስታ ያደራችሁ ሰዎች እግዚአብሔር እንደኔ አያድርጋችሁ ። እንኳን የሐበሻ ጠላቴን ኢየሩሳሌም ዘምቼ ቱርኮችን አስለቅቃለሁ መስሎኝ ነበር ። . . . »

መልዕክተኞቹ ከተራራው ከሰላምጌ ተነሥተው ሁለት ሰዓት ከተጓዙ በኋላ እሮጌ እንግሊዝ ጦር ሠፈር ደረሱ ። ዝናራል ናፒዩርና ሹማምንቱ ለሦስቱም መልካም አቀባበል

አደረጉላቸው ። ዋናው መሪናፒዬር ደጃች ዓለሜን ወደ ግል ድንኳኑ አስገብቶ እጉኑ በማስቀመጥ የአክብሮት መስተንግዶ ካደረገላቸው በኋላ ፣ ወደ ውጭም አውጥቶ በዝሆን የተጫነውን የጦር መሣሪያና ወታደራዊ ድርጅቱን በዝርዝር አሳያቸው ። ይኸውም አግቸዩው ሁኔታውን አይተው ቴዎድሮስን መከረው እንዲያግባቡ ነው ።

በርሱ በኩል ያለውን የዕርቅ አሳብ በቃል ለመልክተኞቹ ከገለጸ በኋላ ፣ እርሳቸው ለላኩት የጽሑፍ መልእክት እርሱም በጽሑፍ አሥፍሮ የመልሱን ደብዳቤ ሰጥቶ መልሶ ላካቸው ። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው ። «ግርማዊነትዎ በጉብዝና ተዋግቷል ። የተሸነፉትም ከርስዎ የበለጠ የእንግሊዝ ኃይል ተጽዕኖ አድርጉብዎ ነው ። ዳግመኛ ደም እንዳይፈስ የኔ ፍላጉት ነው ። ስለዚህ የግርማዊነትዎ ፈቃድ ሆኖ ራስዎን ለእንግሊዝ ንግሥት ቢያስገዙና (ቢገቡ) በእጅዎ ያሉትን አውሮፓውያን በደህንነት በዛሬው ቀን ለእንግሊዝ ጦር ሠፈር ቢያስረክቡ ፣ ለራስዎና ለመላው ቤተሰብዎ ክብር ያለው አያያዝ እንደምና ደርግ ዋስትና እሰጣለሁ ። (ቃል እሰጣለሁ) »

ይኸን ደብዳቤ አዘጋጅቶ ከሰጣቸው በኋላ ፣ ለደጃዝማች ዓለሜ በአስተርጓሚ አማካይነት እንደዚህ አላቸው ። «ንጉሡ ራሳቸው ወደኛ መግባት አለባቸው ፤ ይኸን ጥያቄያችንን ሳይቀበሉ የቀሩ እንደሆነ ያዩትን የመድፍና የእርም ስትሮንግ ጠበንጃ ወደ ተራራው ልከን እንወጋቸዋለን ።* በዚህ ጊዜም አንድ ወታደር ሊያመልጠን አይችልም ። » (1) ይኸንንም የማስፈራሪያ ቃል ጨምሮ በላካቸው ጊዜ የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳም ወደላይ አምባው ለመላክ ፈቃደኛ መሆኑን ነግሮ አሰናበታቸው ። መልክተኞቹም ወዳ፤ ቴዎድሮስ ተመልሰው ደብዳቤውን ፍላድና ወልድሜየር ወደ አማርኛ ተርጉመው በተነበበላቸው ጊዜ ፣ «የክብር አያያዝ ይደረግላቸዋል

---

* በ1810—1900 ዓ. ም. መካከል የነበረ የጦር መሣሪያ መሐንዲስ ነው ። አሁን ናፒዬር የተመካበት ጠበንጃ በርሱ አሳብ የተሠራ ዘመናዊ ጠብመንጃ ነው ።

1 Record of the Expedition to Abyssinia - Holland - Vol. II pp 39-42 Armstrong



ማለት ምን ማለት ነው፤ እንደ ምርኮኛ አክብረን እንይዛቸዋለን ማለት ነው ወይስ ከጠላቶቼ ጋር (*) በማደርገው ጦርነት እንረዳዎታለን ማለት ነው?» ሲሉ ጠየቁ ። መልእክተኞቹ ግን በደብዳቤ ከተገለጸው በቀር ጠቅላይ አዛዡ ዝርዝር ሁኔታ አል ነገሩንምና ግርማዊነትዎ በደብዳቤ ሊጠይቁት ይችላሉ ብለው መለሱላቸው ።

---

* ባሁን ሰዓት ጠላቶቼ የሚሉዋቸው ተድጥም የሸፈቱባቸውን አሁንም እንዋጋም ብለው የሸፈቱትን መሆን ነው ።

# ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

## ሁለተኛው የዐፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤና የእስረኞቹ መለቀቅ

ያለፈው የመዠመሪያው ደብዳቤ አድራሻውን ለማንም ሳያደርጉ ደብዳቤው ግን ለናፒዬር ደርሶት ካወቀው በኋላ ፡ ደግሞ እንደገና አከታትለው በፍላድና በደጃች ዓለሜ እጅ ሁለተኛ ደብዳቤ ፡ ለፋሲካ የሚሆን ብዙ ከብትና በግ ጨምረው ላኩ ለት ። የደብዳቤው ፍሬ ነገር ከዚህ እንደሚከተለው ስፍሯል ።

«በስመ አብ...... ይድረስ ለገናናዋ የእንግሊዝ ንግሥት ተወዳጅ አሽከር . . . ግንኙነታችን በድንገት ስለሆነ ፡ በስ ምህ ልጽፍልህ አልቻልኩም ። (*) የትናትናውን ደብዳቤ ላንተ በመላክ ስለ ተጣላሁህ ተጸጽቻለሁ ። (**) የኔ ወዳጅ ! የውጊያች ሁን ሁኔታ የጦር ድርጅታችሁንና የወታደራችሁን ሥነ ሥር ዓት ተመልክቼ ፡ የኔ ሕዝብ ትእዛዜን መፈጸም ስላቃታቸው እዘ ንሁ ! ወታደሮቼንም ብገድልም ፡ ብቀጣም ወደ ጦርነቱ አል ተመለሱም . . . የወዳጄን የፊታውራሪ ገብርዬን ሬሳ . . . እን ዲቀበር በመፍቀድህ ምስጉን ነህ ። ከኔ ወገን ወዳጄን ዋልድ ሜየርን ጭምር አውሮፓውያኑን በሙሉ እንድለቃቸው ጠይ ቀኸኛል ፤ እሺ ይሁን ፡ ሁሉም ይለቀቃሉ ። ነገር ግን አሁን ካንተ ጋር ወዳጅ ስለ ሆንን ፡ እኔ የእጅ ጥበበኛ ስለምወድ ባዶዬን እንዳታስቀረኝ ።» (1)

ይህ ሁለተኛው ያማርኛው ደብዳቤ እንደ ደረሰ አቶ ሳሙ ኤል ጊዮርጊስ ከአማርኛ ወደ ዐረብኛ ከተረጐመው በኋላ ፡

---

- (*) ባለፈው ደብዳቤ ሮቤርት ናፒዬር ብዬ አልጻፍሁልህም ማለታ ቸው ይመስላል ።
- (**) የፊተኛው ደብዳቤ ለሕዝባቸው በሮሮ መልክ የጻፉትን ለርሱ በመላካቸው ፡ ለርሱም የሠነዘሩት አነጋገር ወቀሳ ስላለበት ነው ።

1 Reco rd ..........pp. 40 - 41

ራሳም ካፄ ቴዎድሮስ ተፈቅዶለት በዚህ ጊዜ ነጻ ሆኖ እንግሊዝ ጦር ሠፈር ነበርና እርሱ ደግሞ ከዐረብኛ ወደ እንግሊዝኛ ተርጕሞ ለናፒዬር ቀረበለት ። ናፒዬር የደብዳቤውን አሳብ ከተረዳ በኋላ ፥ እስረኞቹን ለመፍታት እሺ ማለታቸው ደስ አለው ። ነገር ግን ፥ በእጁ እስኪገቡለት ድረስ በሙሉ ሊተማመን አልቻለም ።

ስለዚህ ፥ ዐፄ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ያለምንም ውለታ እስረኞቹን ፈትተው ለመላክ ወሰኑ ። ውሳኔውን በመጀመሪያ ሰምቶ የምሥራቹን ለወገኖቹ የነገረ ማዬር የሚባል የጀርመን ተወላጅ ነው ።

ነገር ግን ፥ የዚህን ወሬ እሑድ የሰሙት እስረኞች ግማሾቹ በደስታ ሲዋጡ ፥ የቀሩት ዐርብ በደረሰው በፊታውራሪ ገብርዬ ሞትና በጠቅላላው በእንግሊዝ ጦር በተፈጸመው ጥቃት ምክንያት ንጉሡ ትፈታላችሁ በሚሉ ሰበብ አውጥተው ይፈጁናል የሚል ጥርጣሬ አደረባቸው ። ይሁን እንጂ ፥ ንጉሡ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ የዕርቁን መንገድ አገኛለሁ በሚል ተስፋና እስረኞቹን ካገኘ ወዳገሩ ይሔዳል በሚል እምነት ለመልቀቅ ስለ ወሰኑ ፥ የእስረኞቹን ጠባቂ ራስ ቢሠውርንና ቢቶደድ አሰኔን አስጠርተው በነርሱ አማካይነት «አሰናብቻችኋለሁና ዛሬውኑ ወደ ወገኖቻችሁ ሒዱ ፤ ዕቃችሁን ነገ ሰው ልካችሁ ታስወስዳላችሁ» የሚል መልእክት ላኩባቸው ። ([1])

የእስረኞቹ ጠቅላላ ወንዱም ሴቱም ፥ ሕጻናቱም ቍጥራቸው ወደ 72 መድረሳቸውን ዶክተር ብላንክ ሲያረጋግጥ ፥ ያገራችን ጸሐፊ በሚሰጡት የአውሮፓውያንና የክልሶች ቍጥር ዝርዝራቸውን በሃምሳ ላይ አቁመውታል ። ከፈረንጆቹ ውስጥ የእንግሊዝ ፥ የጀርመን ፥ የፈረንሣይ ፥ የስዊስና የኢጣልያን ተወላጆች ይገኙባቸዋል ። ይኸው ያገራችን ጸሐፊ ከነዚህ እስረኞች ውስጥ ደንበኞቹ እስረኞች ቍጥራቸው ከ10 እንደማይበልጥ ፥ 8 የሚሆኑት በልዩ ልዩ የእጅ ሥራ የተሠማሩ ፥ ማርቲን ፍላድና ባለቤታቸው ፥ አስተማሪዎች መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ ፥ የቀሩት ክልሶቹ ግማሾቹ ዶክተር ሺምበር የሚባሉ የጀርመን ተወላጅ

(1) La Campagna Ing.... pp. 64 - 65



(ሽምፐር ዊልሄልም) ብዙ ዘመን በኢትዮጵያ የተቀመጡት ከኢትዮጵያዊቷ ከወይዘሮ ምርጺት የወለዷቸው ወንድ ሽምፐር እንግዳ እሸት ፥ ሴቶች ሽምፐር ጣይቱ ፥ ሽምፐር ትብለጥ ፥ ሽምፐር ደስታ ፥ እንደዚሁ ያፄ ቴዎድሮስ ባለሟል የነበረውና የጋረድ አሽከር የገደለው ሊቀመኳስ ዮሐንስ ካንዲት ኢትዮጵያዊት የወለዳቸው ቤል የውብዳር ፥ ቤል በለጠች ፥ ቤል ሉዊዛ የሚባሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ። ([1])

የውጭ አገር ሰዎች እነ ማርክሃም ፥ እነ ራሳም እንደ መዘገቡት የውጭ አገር ሰዎቹ ቍጥር እስከ 61 ፥ ያገር ተወላጆቹ የነርሱ የአገልጋዮቹ ቍጥር እስከ 187 መድረሱን ያመለክቱና የአውሮፓዎቹን ስም ከዚህ እንደሚከተለው ዘርዝረውት ይገኛል ።

ቆንሲል ካሜሮን ፥ ጸሐፊው ብራንስ ፥ አሽከሮቹ ጴጥሮስ ፥ የማክሬር ፥ ሜክለቪ ፥ ሆርሙዝድ ራሳም ፥ ጓደኞቹ ብራንክና ፕሪዶ ፥ ሚሲዮናውያን ስቴርን ፥ ሮዜንታል ከነሚስቱ ፥ ስተደጃር ፥ ብራንዴይ ። የእጅ ጥበበኞች ወልድማዬርና ባለቤቱ ፥ ስአልሙለር ፥ ፍላድና ባለቤቱ ፥ ቤንደርና ባለቤቱ ፥ ዜንደርና ባለቤቱ ፥ ማየር ፥ ሚስ ዚዩግለን ፥ ሞሪስ ሀል ፥ ቡርጉድ ፥ የእጅ ሠራተኞች አቶ አሊጋዝ ፥ የዕፀዋት ሊቅ ሺምበር እና ጓደኞቹ ኤስለርና ሺለር ፥ ባርዴል (ፈረንሣዩ) ፥ እንግዳ የሺምፐር ልጅ ፥ ዦህን ፓርኪንስ ፥ ካሣ ዘንዳር ፥ ያዕቆብ ሞሪስ ፥ ዮሐንስ ማየር ፥ ጐቴልፍ ቤንደር ፥([2])

የሆነ ሆኖ ፥ በራስ ቢሠውር መሪነት እስረኞቹ ከሚቀመጡበት ከላይ ከመቅደላ አፋፍ ከእስር ቤት እየተንጋጉ ዐፄ ቴዎድሮስ ወዳሉበት ወደ ፋላ (ፋህላ) ሲመጡ ግራና ቀኝ የሚመለከታቸው ወታደር ግማሹ ፥ «ይኸን ሁሉ ጣጣ ያመጡብንን ፈረንጆች መፍጀት ነበር» ሲል ሌላውም በመሰለው ተናገረ ።

1 ፋዜላ..........ገጽ 47— 48

2 The Emperor and the Quetion of Foreign Artisans in Ethiopia R. Panhurest - pp. 233 - 234 - A History of the Abyssinian Exp C. Markham, p. 340.

የሆነ ሆኖ እስረኞቹ በመጨረሻ ከንጉሡ ፊት ደረሱ ። ንጉሡም
በፈገግታ ተቀበሏቸው ። ነገር ግን ፣ ከመካከላቸው ቆንሲሉ ካሜ
ሮን የፀሐዩ ሐሩር አዳክሞት ስለ ነበረ ፣ መቆም አቅቶት ሲንገዳገድ
አይተው ንጉሡ «ምን ሆኗል?» ብለው ጠየቁ ። «ትንሽ ጤና
አጥቷልና እንዲቀመጥ ቢፈቅዱለት?» የሚል ጥያቄ ከእስረኞቹ
ወገን ሲቀርብላቸው ፣ እንዲቀመጥ ፈቅደው ካንዳንዶቹም ጋር
በተለይ ከሚሲዮናዊው ከስቴርን ጋር ፣ «ምነው ጠጉርህን አሳ
ድገህ ሹሩባ ሥራ አስመሰልከው» እያሉ በፈገግታ ይነጋገሩ
ዠመር ። በኋላም ከብዙው አጃቢ ሕዝብና እስረኛ ለየት ብለው
እነ ካሜሮንን ጠርተው ፣ «በጦርነቱ ጊዜ (የእሮጌው) አደጋ
እንዳያገኛችሁ እሁነኛ ሥፍራ እንድትቀመጡ አድርጌያለሁ»
ብለው ካጨዋወቷቸው በኋላ በሰላም አሰናበቷቸው ።

በተለይ ለሁሉም እስረኞች እንደ በላይ የሚቆጠረውን
ምንም ቢያስሩት እንደ ወዳጃቸው ቆጥረው ፣ አሁንም ከጄኔራል
ናፒዬር ጋር በሚደረገው የመላላክ ጊዜ ሳይለይ እስረኞቹም
በሰላም እንዲለቀቁ አበክሮ ይጣጣር የነበረውን ምስተር ራሳምን
በእጅ ጨበጣ አክብረው አሰናበቱት ። ዶክተር ብላንክ ወዳገሩ
ተመልሶ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ፣ «እኛ እስረኞቹ ከፊታቸው
እልፍ ካልን በኋላ መልሷቸው ይሉ ይሆን እያልን እየሠጋን
ስንጓዝ . . . ራስ እንግዳ ‘እነዚህን ነጮች እንግደላቸውና እን
ሙት ፣ ወይም እንጥፋ’ አሉ ። ቴዎድሮስ ግን ፣ ‘የማትረባ አህያ!
በነዚህ በመጨረሻ የሁለት ቀኖች ውስጥ ብዙ ሰው አልገደል
ህም (አልገደልንም ?) አሁን ደግሞ ፣ እነዚህን ነጮች ገድለን
መላው አበሻን በደም ምልክት ማልበሱ ምን ይረባል ?’ ብለው
መለሱሉት» ሲል ያረጋግጣል ። (*) ይኽ አባባል ግን ፣ እን
ደዚሁ ሰው ፈጥሮ ያወራው እንጂ ራስ እንግዳ በፍጹም አለ
መናገራቸውን ራሳም በበኩሉ ያረጋግጣል ። ይሁን እንጂ ፣ ንጉ
ሡና ራስ እንግዳ የተለዋወጡት አሳብ ከእውነት የራቀ አይመ
ስልም ። ራሳም የሁለቱን የአሳብ አለዋወጥ በወሬ ካልሆነ
በቀር ራሱ ሊረዳው አይችልም ።

---

* ምናልባት የራስ እንግዳን ጥያቄና ያፄ ቴዎድሮስን ይኽን የመሰለ
ውን መልስ ፣ ከሰላምጌ ጦርነትና ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ ከምር
ኮኞቹ አንደበት ሰምቶት ይሆናል ።



የሆነ ሆኖ ፣ ቆንሲሉ ካሜሮንና ራሳም ከፊት ሆነው ወን
ዱም ሴቱም እየፈራም ፣ እየተባም ያፄ ቴዎድሮስን ሠፈር ወደ
ኋላው ገልመጥ እያለ እያየ ፣ ቁልቁለቱን ወርዶ ወደ እንግሊዝ
ሠፈር ተጠጋ ። በዚህም ጊዜ የእንግሊዝ ወታደር ወደላይ ከፍ
ብሎ ግራና ቀኝ በየሜካው ተሰግስጎ ሁሉም ጠበንጃውን ደግኖ
ይጠባበቅ ነበር ። እስረኞቹም በተለያየ መንገድ ነበር የሚጓ
ዙት ። ይኸም ግማሹ አደጋ ቢያገኘው የቀረው ሊያመልጥ ይች
ላል በሚል ጥንቃቄ ይመስላል ።

ነገር ግን ፣ ያለምንም ችግር እስረኞቹ ቁልቁለቱን ሲወርዱ
ብዙ ዘመን ጐንደር በመቀመጥ የአማርኛ ቋንቋ የሚያውቀው
የኛዎቹ ባሻ ፈለቀ የሚሉት ፣ በእንግሊዞቹ ዘንድ ካፒቴን ስፒዲ
የሚባለው የፊታውራሪ ገብርዬን ያማረ የጦር ልብስ ፣ ያንበሳ
ለምድና ጐፈር ለብሶ ፣ ቆባቸውን ደፍቶ የርሳቸውን የጭናቸ
ውን ፈረስ ተቀምጦ ፣ እስረኞቹን በማስተናበር ተቀብሎ እየመራ
ወደ ጄኔራል ናፒዬር ሠፈር ሲመራቸው ፣ ከርሱና ከእስረኞቹ
ጋር አሁንም ደጃች ዓለሜና አቶ ሳሙኤል ጊዮርጊስ አልተለ
ዩም ። በበኩሉ ጠቅላይ መሪው ናፒዬር በጦር አለቆቹ እንደ
ታጀበ ወታደሩ እንደ ተሰለፈ ፣ ሙዚቃና ወታደራዊ ጥሩምባ
እየተነፋ በደስታና በፈገግታ ተቀብሎ ሁሉንም እየጨበጠ ካነ
ጋገረ በኋላ ፣ የቀሩትን በየሠፈሩ አከፋፍሎ ልኮ ዋነኞቹ ባለ
ሥልጣኖች የነበሩትን ቆንሲሉን ካሜሮንንና ሆርሙዝድ ራሳ
ምን ወደራሱ ድንኳን ይዟቸው ገባ ።

አምስት ዓመት በሥጋት ሲያወዛግብ ፣ መልክተኞች ሲያ
መላልስና ብዙ ደብዳቤ ሲያጻጽፍ ፣ ለጐንደር ከተማ ፣ ለደብረ
ታቦር ዘረፋና እልቂት ሰበብ ፣ ላሁኑ ዘመቻ ፣ ለገብርዬም ፣ ለቴዎ
ድሮስም ውድቀትና ሞት ምክንያት የሆነው የእስረኞች ጉዳይ
በዚህ ዐይነት ፍጻሜ ሊያገኝ ችሏል ።

# ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

## የዕርቁ ተስፋ መፍረስ — የፋላና የሰላምጌ ጦርነት
## የዐፄ ቴዎድሮስ ፍጻሜ

ጄኔራል ናፒዬር ፣ በዐፄ ቴዎድሮስ ትእዛዝ የተፈቱትን ወገኖቹን እጅ ካደረገ በኋላ ፣ በእስረኞቹ ላይ አደጋ እንዳይደርስ በጥንቃቄ ረገብ አድርጎት የነበረውን ጥያቄ አሁን እንደገና ጠበቅ ሲያደርገው ይታያል ። እስረኞቹን መቀበል ብቻ ሳይሆን ንጉሡንም ከንጉሠ ነገሥታዊ ሥልጣናቸው በማስለቀቅ ለመበቀል ይነሣል ።

እንግሊዞቹ አመጣጣቸውም ከዚህ በፊት እንዳልነው በደንበኛ የዘመቻ ድርጅት በገንዘብ ፣ በስንቅ ፣ በመድኃኒት ፣ በማጓጓዣ ከብት ተሰናድተው ፣ ለያንዳንዱ ጉዳይ ለወታደርነቱ ፣ ለፖለቲካው ፣ ለሰለላው ፣ ለስንቁ ፣ ለጤንነቱና ለመንገዱ ሥራ ኃላፊ አድርገው ፣ ለብዙ ቀን ጦርነት ተዘጋጅተው መጥተው ስለ ነበረ የስቅለት ለት ዐርብ በአሮጌ በፊታውራሪ ገብርዬ የተመራውን ጦር ከደመሰሱ በኋላ ፣ በጦር በኩል ያላቸውን ኃይል አሳዩ ። በእርግጥም ዐፄ ቴዎድሮስ ጦራቸው እታች በመድፍና በጠበንጃ ሲጠቃ የእንግሊዝ ጦር በሥነ ሥርዓት መዋጋቱን ፣ የርሳቸው ጦር ተመጣጣኝ ባልሆነ ስልት እየተዋጋ በኋላም መዘበራረቁን ከላይ ከፋላ ሥላሴ በመነጥር እያዩ በመጨረሻም ጦራቸው መፍረሱንና ገብርዬ መሞቱን ፣ በጠቅላላው ኃይላቸው ከእንግሊዝ ማነሱን የተረዱት ከዚህ ቀን ጦርነት በኋላ ነው ። ከአምስት ዓመት (1855 - 60) መላላክና የዲፕሎማሲ ትግል በኋላ ፣ ለዚህ ሁሉ ጥፋት ሰበብ የሆኑትን እስረኞች የለቀቁት ከዚህ ከአሮጌ ጦርነት ወዲህ ነው ።

ምንም እንኳን ፣ በፊተኛው የናፒዬር ደብዳቤ ላይ «ለእንግሊዝ ንግሥት ቢገቡ በክብር እንይዝዎታለን» የሚል ቃል ቢኖርበትም ፣ ባንድ ወገን የመልእክተኞቹ የለሰለሰና የማግባባት

እነጋገር ፣ በሌላው ወገን ፣ «የክብር አያያዝ እናደርግልዎታለን» የሚለው አሳብ በአዕምሮዋቸው ውስጥ እየተመላለሰና ወደፊትም የሰላም መንገድ አግኝቼ ሀገሬን አሠለጥናለሁ የሚል ተስፋ እንዳደረባቸው ይታወቃል ። በሁለተኛው ደብዳቤያቸው ላይ ፤ «እንግዴህ ወዳጅ ስለሆንን እነዋልድ ሜዬርን ወዳጆቼን ወስደህ ያለ እጅ ጥበበኛ እንዳታስቀረኝ» ብለው ሲጽፉለት እስረኞቹን ካገኘ ወዳገሩ እንደሚመለስ ነበር የታያቸው ።

ዤኔራል ናፒዬር ግን ፣ ለደጃች ዓለሜ ንጉሡ በግድ በሰላም እጃቸውን መስጠት እንዳለባቸው ፣ ያለዚያ የእንግሊዝ ጦር ወደ ሰላምጌ ወጥቶ እንደሚዋጋ አጥብቆ በማስረዳት አስጠንቅቋል።[1]

በዚህም ጊዜ ዐፄ ቴዎድሮስ በሰሜንና በምዕራቡ ወገን የእንግሊዝ ጦር ስለ ተጫናቸው ፣ በምሥራቅ ደቡብ በተለይ ቃፊር በር በሚባለው በኩል አመለጡ ወይም ሊያመልጡ ነው የሚል ወሬ ስለ ተሰማ ፣ ቀድሞውኑ የፖለቲካው መሪ ኮሎኔል ዊሊያም ሜሬዊዘር አከበር ዐሊ ከሚባለው የዋጅራቱ ተወላጅ ጋር ግንኙነት አድርጎ በርሱ አማካይነት ገንዘብም ፣ ልዩ ልዩ ስጦታም ለወሎ ባላባቶች ለነወይዘሮ መስተዋት እየላከ በመዛመድ በነርሱ ክፍል ቴዎድሮስ እንዳያመልጡ ጠንክረው እንዲጠባበቁ አድርጓል ። በእውነትም አምልጠው ይሆን በሚል ጥርጣሬ እጃቸውን ይዞ ላመጣ 50,000 ጥሬ ብር እንሰጣለን ብለው በገሃድ ቃል ገብተዋል ።[2]

ሚር አከበር ዐሊ አማርኛም ፣ ዐረብኛም ከኦሮምኛ ጋር ደርቦ ስለሚያውቅ በስለላ ረገድ ብቻ ሳይሆን የራያና የአዘቦ ፣ የዋጅራትና የወሎ ኦሮምኛ የሚናገረው የእስልምና ሃይማኖት የያዘው ክፍል ከእንግሊዝ ጦር ጋር እንዲተባበርና ቴዎድሮስን እንዲያጠቃ በብዙ መርዳቱን ራሱ ናፒዬር ለበላዮቹ በጻፈው ራፖር መስክሯል ።[3] የወሎ ሕዝቡም ፣ መኳንንቱም ባለፈው ጊዜ ባፄ ቴዎድሮስና በጦራቸው ብዙ ጉዳት ስለ ተፈጸመበት ፣ የእንግሊዝን ጦር አመጣጡንና ባፄ ቴዎድሮስ ላይ መዝመቱን አልተቃወመም ።እንዲያውም ተደስቷል ማለት ይቻላል ።

1 Record..........pp. 44-46
2 Idem..........pp. 51-52
3 Field Marchal Lord Napier of Macdala..........A Memoir by his son.......... pp. 234-235.



ስለዚህ ሚር አከበር ዐሊ ወደ ወሎዋ ባላባት ወደ ወይዘሮ መስተዋትና ወደ ሌሎችም ባላባቶች ዘንድ ስጦታም ፣ መልእክትም ይዞ ሔዶ ተወያይቶ ለናፒዬር እንደ አው. ቀ. 16 ሚያዝያ 1868 ዓ.ም (ጦርነቱ ካለቀ በኋላ) በጻፈው ሰፊ ራፖር የወሎ ሕዝብ እንደ ተቀበለው ፣ ባለፈው በደረሰበት ሥቃይ ባፄ ቴዎድሮስ ላይ ያለውን ጥላቻና በማናቸውም ከእንግሊዝ ጦር ጋር ለመተባበር ያለውን ስሜት ሲገልጽ ፣ በተለይ መስተዋትና ወጣቱ ልጇ ይማም አህመድ የሎጎት መቀመጫቸውን ለቀው ወደ መቅደላ በመጠጋት ሹማምንቶቿና ወታደሮቿ ቴዎድሮስ ሊያመልጡ የሚችሉበትን የቃፊር በር እንዲጠብቁ ማድረጓን በዝርዝር ገልጿል ።

እስረኞቹ ከተመለሱ በኋላ ፣ የእንግሊዝ ጦር አዛዥ በጽሑፍም በላከው መልእክት በቃልም ለደጃች ዓለሜ እንደ ተናገረው ፣ አንደኛ ዐፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን እንዲሰጡ ፣ ሁለተኛም የታሰረውን ሁሉ የኢትዮጵያ መኳንንት በሙሉ እንዲለቁ በቁርጥ ከላከባቸው ወዲህ ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ በመጨረሻው የወሰኑት ምርጫ እየተዋጉ መሞት ነው ።

የሰኞውን የጦርነት ጉዳይ ያገራችን ጽሑፍ እንደዚህ ሲል የመዘገበው በግልጽ ይነበባል « . . . ራስ መሸሻ ያፄ ቴዎድሮስ ልጅ እሑድ ገቡ ፣ አባታቸውን ትተው (*) እንግሊዞችም እሑድ እስሮችን ተቀብለው አደሩና በነገታው ሰኞ (የፋሲካ ማግሥት) ፈረሶችን ጥሬ አብሉ ተብሎ ጥሩምባ ተነፋ . . . ጥሬ ከተጨረሰ በኋላ ፣ በስድስት ሰዓት ፈረሶች የእግራቸው ችንካር ይቸነከር ነበር ። . . . በቶሎ ሁሉ ተጫነና አንድ ቄስ ጸሎት ያደርግ ነበር ። መኳንንቱም ሁሉ የጦር ልብሱን ለብሶ ጉራዴያቸውን እንደ ታጠቁ ተምበርክከው ጸሎት አደረጉ . . . ጥሩምባ ተነፋ ። ፈረሰኞች ባንድነት ከፈረስ ወጡ ፤ እግረኛም በየሰልፉ ሪጋ(**) ሆኖ ግጥም ብሎ ቆመና በየሰልፍህ ተጓዝ ያለው ጊዜ ፈረሰኛው ባንድ ወገን ፣ እግረኛውም ባንድ ወገን ጥሩምባው ምድር እየፈነቀለ ወደ መቅደላ አምባ ባቀበቱ ይጓዝ ዠመር ።

* ወደ እንግሊዞች ማለቱ ነው ።
** ጸሐፊው ሪጋ የሚለው በኢጣልያንኛ መስመር ለማለት ነው ። የኢጣልያ ቋንቋ የሚያውቅ ኤርትራዊ መሆን አለበት ። «ን» የሚባለውንም ሳቢዘር አያደርግም ።

ንጉሡም መምጣቱን ባዩ ጊዜ የአምባው በር ጠባቆች በሩን ትተው ወደታች ከሜዳው ወርደው ከነበሩት ሰዎቸው ጋር ተሰልፈው ቆዩ ። መድፎቻቸውንም ካምባው ውጭ አዝግበው ነበር ።(*) እንግሊዞች ቀረብ ሲሉ ተኰሱባቸው ። ንጉሡም ባለቤታቸው (ራሳቸው) በሐመር ፈረሳቸው ወጡና አንድ ጠበንጃ አነገቱ ፤ አንድ ጠበንጃም በእጃቸው ይዘው ማሕል ለማሕል ሔደው ወደ እንግሊዞች ተኰሱ ። የእንግሊዝ የጦር አለቃ አትተኩሱባቸው ብሎ አዞ ነበር ይላሉ ። ዐጤ ግን ፣ ከፈረሴ ደንደስ እሞታለሁ እያሉ እያመላለሱ ይተኩሱ ነበር ፣ ፈረሳቸው እስኪደክም ድረስ ።እንግሊዞችም እርሳቸውን ትተው ወደ ሌሎች እየተኮሱ ወደ አምባው ተጠጉ . . . ራስ እንግዱና(**) ወንድማቸው አዛዥ ፈንታ ሞቱ ። ንጉሡም ወደ አምባው ገቡ ። እንግሊዞችም ተከታትለው ወደበሩ ገቡ ። መድፉም እጅታ አደረጉት ። (***) በሩንም የንጉሥ ጠባቆች ለቀቁትና ገባ ብለው ለንጉሥ ተናገሩ ። ንጉሥም ሽጉጥዎን (ሽጉጣቸውን) መዘዙና ባፍዎ (ባፋቸው) ጐርሰው ተኰሱትና ሞቱ . . . » ([1])

በበኩላቸው አለቃ ወልደ ማርያም ዘምሑይ ስለዚህ ጉዳይ ባጭሩ እንዲህ ሲሉ የጻፉት ፣ ከዚህኛው በመሠረቱ የተለያየ አይደለም« . . . ከበሩ ላይ ጥኑ ውጊያ ተዠመረ ።ከእንግሊዝ ወገን አንድ መድፍ ቢተኰስ በሩ ተሰበረ . . . የክረምት ነጐድጓድ መሰለ ። የመድፉና የነፍጡ (የጠበንጃው) ድምጥ . . . በዚህ መካከል የእንግሊዝ ወገን በሩን ሰብሮ ሲገባ ቴዎድሮስ ከላይኛው በር ዐልፈው ተቀመጡ ። በቋንቋው እየተናገረ (እንግሊዙ) ቴዎድሮስን ንጉሡን እየፈለገ ሲቀርብ ሲያዩት ፣ «ይህስ ይዞ አስሮ ሲወስደኝ (ከሚወስደኝ) ሞት ይሻለኛል» ብለው በራስዎ (በራሳቸው) ፈርደው እንደ ዐመፀኛ ጠበንጃ አስወጡበት ። ([2])

የእንግሊዞቹ ጽሑፍ በበኩሉ እንደሚተርከው ፣ ዋናው ጠቅላይ አዛዥ ጄኔራል ናፒዬር ዐፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን

* እያነጣጠሩ ወይም እያለሙ

** እንግዳ

*** መድፉን እጅ አደረጉት ወይም ያዙት ለማለት ነው ።

1 ቀዜላ ያሳተመው ገጽ 48—49

2 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ.......... ገጽ 57—58 ጠበንጃ አስወጡበት የሚሉት ፣ የሽጉጣቸውን ጥይት ጠጥተው ሞቱ ለማለት ነው ።



እንዲሰጡ በደጃች ዓለሜ እጅ የተላከው የዐርባ ስምንት ሰዓት ጊዜ ገደብ ሰዎ ጧት ስላለቀ ፣ ለምክትሉ ለሜዠር ጄኔራል ሻርል ስታቬሌይ ወደ ሰላምጌ ጦሩ ዘምቶ በቅድሚያ ፋላ ሥላሴን እንዲይዝ ትእዛዝ ሰጠው ። ስታቬሌይም ለኰሎኔል ዋላስና ለኰሎኔል ፔን ትእዛዝ አስተላልፎ ኢትዮጵያዊው ጸሐፊ እንደ ጠቀሱት እግረኛውም ፈረሰኛውም ፣ ባለጠበንጃውና መድፈኛው በደንበኛ ተሰልፎ በሙዚቃ ፣ በጥሩምባ እየተሟሟቀ ከግርጌ ከእሮጌ ተንቀሳቅሶ ወደ ላይ ወደፋላ በመውጣት ደንበኛው ጦርነት በዘጠኝ ሰዓት ላይ ተጀምሮ የመድፍና የጠበንጃ ጥይት መሽገው በሚጠባበቁት በኢትዮጵያውያኑ ላይ ይዘንምባቸው ዠመረ ። ነገር ግን ፣ በመሬቱ አቀማመጥ በጉብታና በቋጥኝ ደንጊያ መካከል ኢትዮጵያውያኑ ከተገን ውስጥ ስለ ነበሩ ፣ እንደ መድፉ ተኩስና እንደ ጥይቱ ብዛት ብዙ ጉዳት አላደረገም ።

ቢሆንም ፣ በመጀመሪያው በር ላይ ጥቃት የደረሰባቸው ተዋጊዎች እየሸሹ ወደ እስረኞቹ ሐበሾች የታሰሩበት ሔደው መደባለቃቸውን የ33ኛው ብርጌድ ጦር በሻለቃ ኩፐር እየተመራ በፊቱ ያለውን ተከላካይ ጦርና በፍጥረቱ እንደ ምሽግነት ያለውን ቋጥኛማና ሸለቆማ ሥፍራ በችግር ዐልፎ ፣ ምሽግ ለመያዝ ባደረገው ጦርነት ዘጠኝ የጦር መኰንኖች እንደ ቆሰሉበትና በመጨረሻ ለውጊያ አመቺ የሆነውን ቦታ የእንግሊዝ ወታደሮች ይዘው ማጥቃታቸውን ጸሐፊው ሆላንድ ያወሳል ። ([1])

ከዚሁ እያይዞ የእንግሊዝ ጦር ጠመዝማዛውንና በጣም አስቸጋሪ የሆነውን መንገድ ሁሉ በትዕግሥትና በብርታት ዐልፎ ፣ የእስር ቤት የነበረውን ጭምር ከፍተኛውን የመቅደላን ምሽግ መያዙን ፣ በዚህ ጊዜ ያጼ ቴዎድሮስ ጠቅላላ ጦር ቢታመንላቸው ኖሮ ፣ ከዚህ ቦታ ላይ ብዙ የእንግሊዝን ጦር ለመፍጀት ይችሉ እንደ ነበረ ፣ አሁን ግን ዐርብ የስቅለት ለት እሮጌ ላይ በተደረገው ጦርነት የተዋጋው ጦር ሁሉ ሞራሉ ተዋድቆ ታማኝ ሆኖ እስከ መጨረሻ የተዋጋው ቍጥሩ በጣም ያነሰ መሆኑን ፣ በዚህ ጦርነት የአውሮፓ እስረኞች እንዲፈጁ መክረው የነበሩት ራስ እንግዳ መሞታቸውን ፣ የተረፈውም ጦር መሣሪያውን እየጣለና ምሕረት እየለመነ እጅ መስጠቱን ፣ ምሕረትም የተሰጠው መሆኑን ያረጋግጣል ።

1 Record.........Chap. XIX - pp. 50-56

ስለ ራሳቸው ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ ደግሞ ፣ « . . . ቴዎድሮስ መቅደላ ከገቡ በኋላ በኮሎኔል ሉክ የሚመራው ጦር በተኮሰባቸው ጊዜ ፣ የቤተ መንግሥቱ በራፍ በታላላቅ የቋጥኝ ደንጊያ እንዲካብ (እንዲመሽግ) ትእዛዝ ሰጥተው ራሳቸውም ምሳሌ በመሆን አብረው ይሠሩ ነበር ። በዚያ ውስጥ ከ300 ታማኝ ወታደሮቻቸው ጋር ሆነው በተቻላቸው መጠን ከተከላከሉና እነዚህ ታማኝ ወታደሮቻቸው ስለ ቆሰሉና ራስ እንግዳም ስለ ሞቱ ፣ ተቻኩለው ወደላይ (ላይኛው በር) ወጥተው ለጠላት ዒላማ ይመቻል በማለት በእጀ ጠባብ ላይ ደርበውት የነበረውን በወርቅ ያጌጠ ካባ አውልቀው ላሽከራቸው ሰጥተው ከተዋጉ በኋላ ፣ የእንግሊዝ ጦር መቃረቡን ሲረዱት ለታማኝ ወታደሮቻቸው ፣ 'አምልጡ ፣ ከታማኝነታችሁ ጋር እንድትሸሹ ፈቅጃለሁ (*) እኔ በምንም ሁኔታ በጠላት እጅ አልወድቅም' ብለው ሽጉጣቸውን መዘው አፈሙዙን ወደ አፋቸው ውስጥ አግብተው በመተኮስ ራሳቸውን ገደሉ . . . ያፄ ቴዎድሮስም ተዋጊዎች ግማሾቹ ሸሹ ። የቀሩትም ለእንግሊዝ ጦር እጃቸውን ሰጡ ። ወደ ቃፊር በር ከሸሹት ይልቅ ፣ ለእንግሊዝ ጦር እጃቸውን የሰጡት ነፍሳቸውን አዳኑ . . .» ሲል ይደመድማል ።(1)

አለቃ ወልደማርያም ግን ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ከገደሉና ምሽጉ ሁሉ በእንግሊዞች እጅ ከገባ በኋላ ፣ በእጁ ጠበንጃም ፣ ጦርም ይዞ የተገኘ ብዙ ሰው ማለቁን እንደዚህ ሲሉ ያወሳሉ « . . . ሁሉም በሥልጣን (የእንግሊዝ የጦር መሪ) እጅ ሆነ ። የመቅደላም ወታደር ሁሉ የጦር መሣሪያውን ገደል እየጣለ እጅ ነሥቶ ሲቆም በምጥ እንደ ተያዘች ሴት መሰለ ። ያላወቀ መሣሪያውን ያልጣለ የሚዋጋ መስሎ እጅግ ሰው አለቀ ። ጋሻ ነፍጥም (ጠበንጃ) የያዘውን የእንግሊዝ ወገን እየተቀዳደመ (እየተሽቀዳደመ) በነፍጥ ፈጀው ። . . . በጦር ጊዜ የጦር መሣሪያ . . . ይዞ ወደ ገበያም ፣ ወደ ሰፈርም የሚሔደውን . . . ሲያይ ይገድል ነበረ . . . ደግሞ የሐበሻ ሰው ከዳተኛ ይባላልና አስቀድሞ እንዳይገድለው ይመስላል . . .»

---

* ታማኝነታችሁን ተረድቼዋለሁ ፣ አሁን ግን ራሳችሁን ለማዳን ሽሹ ለማለት ነው ።

1 Record..........pp. 55—57. The Abyssinian Expedition - Roger Action pp. 72 - 74



ከዚሁ እያይዘው እኚሁ የዘመኑ ምሁር በራሳቸው አነጋገር ዐፄ ቴዎድሮስ ሰኞ ሞተው የተቀበሩት ማክሰኞ መሆኑን ካወሱ በኋላ የዚህን ምክንያት ሲገልጹ ፣ « . . . ከንጉሡ ከቴዎድሮስ ጋር የነበሩ የእንግሊዝ ወገኖች የሌሎችም የንጉሡን ከእግር እስከ ራስዎ መልክዎን (መልካቸውን) አስመስለው ስለው ከእንግሊዝ ንግሥት ገብቶ ይኖራል ፣ የሐበሻ ንጉሥ ይህ ነው ለማለት . . . » ብለዋል ።(1) ይኸም ማለት በሞቱበት ቀን ያልተቀበሩት ለሥዕሉ ሥራ ጊዜ ለማግኘት ማክሰኞ ተቀበሩ ማለታቸውን ነው ።

---


1 ሞንዶን ያሳተመው ገጽ 58—59




የፋላ ጦርነት
(ከሮገፎ አክቶን መጽሐፍ)



የመጨረሻውን የፉላን ፣ የሥላሴንና የሰላምጌን ጦርነት የመራው ሜዠር ዤኔራል
ሻርል ስቴቬሌይ
(ከሮዤ አከቶን መጽሐፍ)



ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ሲገድሉ
(ከዶክተር ብላንክ መጽሐፍ)



የእንግሊዝ የጦር መኰንኖች ያፄ ቴዎድሮስን ሬሣ በአድናቆት ሲመለከቱ
(ከሮገፎ አክቶን መጽሐፍ)



የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን መቅደላ በእንግሊዝ ጦር ከተያዘ በኋላ በወታደር ሲጠበቅ
(ከዐሥረኛው ሮያል ኢንጂኔሪንግ ብሪጌድ)



ከመቅደላ ውድቀት በኋላ ወደ ዐፄ ቴዎድሮስ ቤተ መንግሥት የሚያስገባው የቃፊር በር ሲጠበቅ ።
(ከዐሥረኛው ሮያል ኢንጂኔሪንግ ብሪጌድ)




ካፒቴን ስፒዲ (ባሻፈለቀ) ከድሉ በኋላ የፊታውራሪ ገብርዬን የጦር ልብስ
እንደለበሰ
(ከሮገ አክቶን መጽሐፍ)



የመቅደላውን (ፋላና ሥላሴ) ጦርነቶች የመራው ዤኔራል ስቴቬሌይ
(ከሪኮርድ ኦፍ ዘ ኤክስፔዲሽን ቱ አቢሲኒያ)

# የእሮጌን ፣ የሰላምጌንና የመቅደላን የጦርነት ሥፍራዎች የሚያሳይ ካርታ ።




የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት 1974 ዓ.ም

# ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

*ባዒ ቴዎድሮስ ሰውነትና ባሕርይ ላይ አጭር አስተያየት ፤ ስለ ዝግንነታቸው የተደረሰላቸው ግጥም*

ሰውነት ሲባል ፣ ያንድን ሰው አካልና ጠባይን ያጠቃል ላል ። አካል በትክክል በዐይን የሚታይ ፣ በእጅ የሚዳሰስ ስለ ሆነ ፣ ያንድ ሰው ጠቅላላ የአካሉ ቅርፅ ከነአባሉ ይታወቃል ። ቁመቱ ዘርጋዳ ወይም አጭር ፣ ግድንግድ ወይም ቀጫጫ ፣ ፊቱ ሞላላ ወይም ክብ ፣ አለዚያም አራት ወይም ሦስት ማዕዘ ንማ ፤ ግንባሩ ፈጣጣ ወይም ሙሉ አለዚያም የተጠረመሰ ፤ ዐይኑ በግ ያለ ወይም ጨፈንፈን ያለ ፣ አለዚያም መጠነኛ ፤ በዚህ ዐይነት የሰውነታችን አባል ሁሉ ሲበዛም ፣ ሲያንስም ሊለያይ ይችላል ።

ጠባይ ሲባል ፣ 'ባሕርይ ፣ መንፈስ ፣ ዐመል ፣ ስሜት' እያ ልን የምንከፋፍለውን ሁሉ ሲያጠቃልል ፣ ያንዱ ሰው ጠባይ ከተግባሩና ከአነጋገሩ ላይ ተወስዶ እገሌ ሐቀኛ ነው ወይም አድርባይ ነው ፤ እገሌ ግን ፣ ዋሾ ነው ወይም እውነተኛ ነው ብለን በትዝብት ሐተታ ካልሰጠን በቀር ፣ ጠባይ ወይም ባሕርይ እንደ አካል በዐይን ስለማይታይ በቀላሉ ሊጨበጥና ሊታወቅ አይችልም ። በጠባይ በኩል የበጎዉም ፣ የክፋቱም ዐይነት ከአ ካል የበለጠ ብዙ ደረጃ ስለ አለው ፣ እዚህ ላይ ያልተነሣንበትን መተንተን አስፈላጊ አይሆንም ።

የቴዎድሮስን የአካላቸውንና የጠባያቸውን ደረጃ ከየት ኛውም ላይ ለመመደብ ያስቸግራል ። ዐፄ ቴዎድሮስን ለማየ ትም ፣ ለማነጋገርም አብሮ ለመኖርም ዕድል ያጋጠማቸው አለቃ ዘነብና አለቃ ወልደ ማርያም የቴዎድሮስን አጫጭር የሕይወት ታሪካቸውን በተዉልን ታሪካዊ የጽሑፍ ቅርስ ውስጥ የትውልዱ ፣ የዕድገቱ ፣ የጦርነቱ ፣ የድሉ ፣ የምርኮውና

የቅጣቱ ዐይነት ሲዘረዝር፣ የዚህ ሁሉ ባለቤት የሆኑት የአንድነት መሥራቹ የቴዎድሮስ የአካላቸውና የጠባያቸው ዝርዝር የለበትም። ጠባያቸውን እንኳን ከተግባራቸው ላይ ብንማር ለማወቅ የሚናፈቀውን የአካላቸውን አባላት በዘመኑ ከተጻፈ ላይ አንብበን በዝርዝር አናውቅም። በታሪክ አማካይነት ዐውቀ ነው የነቀፍነውንም፣ ያደነቅነውንም መሪ የሰውነቱን ዝርዝር ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ቢቻልማ እንደ ዛሬ ዘመን ድምፁም ተቀርፆ ብንሰማው ምን ያህል ደስታና መገረምን ባተረፈልን ነበር። ቴዎድሮስን በመቅደላ፣ ዮሐንስን በመተማ፣ ምኒልክን በዐድዋ ሲያዋጉ ከነንቅናቄው ደንበኛ መልካቸውን ብናይ፣ ድምፃቸውን ብንሰማ ኖሮ፣ የደስታ ስሜታችን ከፍ ያለ በሆነ ነበር።

ዳሩ ግን፣ መሪዎቹ ራሳቸው ወደ ሃይማኖት እንደሚያደሉ በኢትዮጵያውያን ያጻጻፍ ባህልም ውስጥ ምርቱ በርክቶ የሚታየው ገድሉ፣ ድርሳኑ፣ ስንክሳሩ፣ መልካ መልኩ ሁሉም የመንፈሳዊ ጽሑፍ ነው። የፍልስፍናው፣ የታሪኩ ጽሑፍ ብዛቱ ከመንፈሳዊው በጣም ያነሰ መሆኑን ማንም ያውቀዋል። ለኢትዮጵያውያን አበው ምሁራን ትምህርት ሲባል ከመጽሐፍ ቅዱስ የመነጨው ብቻ መሆኑን ከዚህ በፊት አውስተነዋል። በዚያው በየዜና መዋዕሉ ጽሑፍ ደግሞ ከብሉይና ከሐዲስ ጥቅስ ጋር የሰልፉ፣ የጦርነቱ፣ የድሉ፣ የምርኮው፣ የቅጣቱ፣ የዘረፋው፣ የፉከራውና የሽለላው፣ የግጥሙ ምርት ሲታይ በነዚህ ሁሉ መካከል ያሸናፊውንና የተሸናፊውን መልክና ጠባይ የመዘርዘር ባህል የለንም። ለዚህኛው ክፍል ዋጋ ከሚሰጠው የማይሰጠው ይበልጣል። የዛሬ አንባቢ ለማወቅ የሚናፍቀውን ሁሉ ያለፈ ጸሐፊ በቅድሚያ በዘመኑ ለመገመት አዳጋች ይሆንበታል ማለት ነው። ምናልባት የሰው ልጅ አዕምሮ እየሰፋ ፍላጎቱ እየበዛ በሔደ መጠን፣ የኛም የዛሬው አጻጻፋችን ለሚመጣው ትውልድ መዳረሻ እንጂ በደንብ ላያረካው ይችላል።

ስለዚህ በሥዕልና በቅርፅ ሙያ በሚገባ ያልደረጀን እንደ መሆናችን መጠን፣ በሥልጣኔ በማናቸውም መስክ የተራመዱት ፈረንጆች በእጃቸው ከሣሉልን በፎቶ ወይም በጽሑፍ ዝርዝር ቀርፀው ካወረሱን በቀር፣ ከሐያኛው ክፍለ ዘመን መዠመሪያ በፊት ያሉንን የመሪዎቻችንን፣ የደራሲዎቻችንን መልክ በራሳችን ባለሙያ አማካይነት አናውቅም። ባገር ተወላጅ



ተሥሎ ወደ ጊዜያችን የደረሰው ተሣዩን ለማስደሰት ፉንጋው ሁሉ መልአክ መስሎ፣ አሸብርቆ በቁንጅና ተውቦ ስለሚገኝ ሥዕሉና እውነተኛው የሰውዬው መልክ ላይጋጠም ይችላል። ይኸም በታሪክ ረገድ በየዜና መዋዕሉ ላይ ጸሐፌ ትእዛዙ የየራሱን ንጉሥ ታሪክ በቃለ አጋኖ ያልሆነውን በመጨማመር እንደሚያወድሰው ማለት ነው። የድንጊያ ቅርፅማ ከሥልጡኑ ከአክሱም መንግሥት ውድቀት ወዲህ አልታየም።

በዚህ ሁሉ ምክንያት፣ ላሁኑ የታሪክ ምዕራፎች ባለቤት የሆኑት ያፄ ቴዎድሮስ መልክ ሹሩባ እንደ ተሠሩ የምናየውና ሁላችንም በሥዕሉ የምንጠቀምበት ፈረንሣዮቹ እነ ባውድራን የሣሉት ነው። በሰላሙ ቀን በአንበሳ ተከበው የሚታዩት፣ በጭንቁና በቁርጠኛው ቀን የሽጉጣቸውን ጥይት ቆመው ሲጠጡ ወይም ሽጉጣቸውን እንደ ጨበጡ ተዘርረው የሣሉዋቸው እነ ካንዲና እንግሊዞቹ ናቸው። በዚህም ሳናመሰግናቸው ማለፍ የለብንም።

በነዚህ ሁሉ ሥዕል ላይ ያፄ፣ ቴዎድሮስ ፊት የቁጡና የእልኸኛ መልክ ሆኖ ይታያል። መቅደላ ራሳቸውን ገድለው በወደቁበት ጊዜ ወዲያው የደረሱት እንግሊዞች ሲያዩዋቸው በሬሳቸው ገጽ ላይ ዐይናቸው እንደ ተገለጠ ጥብቅነታቸው፣ ኩሩነታቸው ይነበብ እንደ ነበረ ተጽፏል።[1] ከወታደሮቹ አንዱ እንግሊዛዊ እንደ ወደቁ ሬሳቸውን አይቶ «ጐበዝ ባላጋራ ነው፤ በደህና ልንይዘው (ልናከብረው) በተገባ» አለ።[2]

ፈረንሣዩ ጉዮም ለዣን ያፄ ቴዎድሮስን መልክና ጠባይ እንደዚህ ሲል ይገልጻል። «. . . ካሣ አሁን 46 ዓመታቸው ነው።[*] ቁመታቸው መካከለኛ ሆኖ የሚጫን አካል አላቸው። የመልካቸው ገጥታ ግልጽና አስደሳች ተነቃናቂ[3]፣ . . . ያይን አመለካከታቸው ድምቅና ወጊ[4]፣ ከምሥራቅ ሕዝብ ነጻነት

1 Hist. pol. Coulbeaux pp. 410-411.
2 Idem

* እንደ አው. ቁ. 1866 ዓ. ም. ላይ ማለቱ ነው። በኢት. 1858 ይሆናል።
3 Physionomie ouverte et sympathique..........Expressifs et Mobiles
4 Le regard est vil et percent

የሚሰማውንና ሳገዛዝ የማይበገረውን ሕዝብ ለመግዛት ያላቸው
ጽኑ ፈቃድ እመልካቸው ላይ ይታያል . . . ለሌላው ጉዳይ
ሲጨነቁ ስለ ልብስ አለባበስ እምብዛም ግድ የላቸውም ።

ስለዚህም የውጭ አገር ሰዎች እርሳቸውን ከሕዝቡና ካጌ
ጡት መኳንንቱ ውስጥ መለየት ይደናገራቸዋል . . . በድንኳ
ናቸው ውስጥ (በጉዞ ጊዜ) ያለው ዕቃ ሁሉ ተራ ነው ። በደብረ
ታቦርና በመቅደላ መኖሪያ ቤታቸው ከሕንድና ከፈረንሣይ
አገር የመጡ የሐር አልባሳት ይታያሉ . . . ። በጠባይ በኩል
ልዝብነት የተበረዘበት ኃይለኛ — ይልቁንም ኃይለኛ . . . ኩሩ
ሆነው የተወለዱ . . . ትንሽ ወደ ደስታ ያዘነበሉ ፤ ቁጡ (ግል
ፍተኛ) . . . ይሰክራሉ ተብሎ በከንቱ ታምተዋል ፤ . . . አይ
ደለም . . . እንዲያውም ቁጥብ ናቸው ። ከመብል ይልቅ መጠጥ
በዛ ያደርጋሉ ። ነገር ግን ፤ እስከ ስካር አይደርሱም ። ከመዠመ
ሪያ ሚስታቸው ከተዋበች በቀር ሴቶች በርሳቸው ላይ ክብደት
የላቸውም ።(1) . . . » ካለ በኋላ ፤ ከዚያ ዐለፍ ብሎ ስለ ዕው
ቀታቸው « . . . በስብሰባ ላይ ደስ የሚያሰኝ ቃል አላቸው . . .
የቀለም ሰው ናቸው . . . የአማርኛ አጻጻፋቸው ልዩ መሆኑን
ዳኞቹ አረጋግጠውልኛል . . . » ሲል ዘርዝሯል ።(2)

በቅርብ የተመለከታቸው ዶክተር ብላንክ « . . . ከብዙ
ዎቹ አበሻዎች ጠቆር ያሉ ጠይም ፤ አፍንጫቸው ደፍጠጥ ፤
አፋቸው ሰፋ ፤ ከንፈሮቻቸው ትንንሽ ጠጋ ፤ ቀጠን ያሉ . . .
በወታደርነታቸው የተመሰገኑ . . . ጐድጐድ ያሉት የጥቋቁር
ዐይኖቻቸው አገላለጥ አስደንጋጭ ሲሆኑ ፤ በሰላም ጊዜ ደስ የሚ
ያሰኙ ፤ የሰውን ፍቅር የሚያስገኙ . . . በተቆጡ ጊዜ ደግሞ
በርበሬ መስለው የሚያስደነግጡ ናቸው» በማለት አመልክ
ቷል ።(3)

ደግሞ ብዙ ጊዜ አብሮአቸው የኖረው ከካሜሮን በፊት
የእንግሊዝ ቆንሲል የነበረው ፕሎውዴን ፤ «የቴዎድሮስ ጉድ
ለት ፤ ቁጡነታቸውና የማይበገረው ኩራታቸው ነው» ሲል ፤

1 Theodore II Le Nouvel Empire D'Abyssinie pp. 181-183
2 ለግን ገጽ 187
3 ዳኘው ወ/ሥላሴ ምዕ. 1



ሌላው ዊልሄም ሺምበር የሚባለው የዕፅዋት ጀርመናዊ ዶክ
ተር «ቴዎድሮስ ከግልፍተኝነታቸው በቀር ከፍ ያለ አስተያየት
ያላቸው ናቸው» በማለት ሁለቱም የለግንና የብላንክን አባባል
አጽድቀዋል ።(1)

ያገራችንም ሰዎች ልዩ ፍጡርነታቸውን ለመግለጽ የማይ
ጨበጡ እሳት ናቸው እስከ ማለት ደርሰዋል ። የእንግሊዝ ጦር
በአሮጌ ሜዳ በፊታውራሪ ገብርዬ የሚመራውን ያፄ ቴዎድሮስን
ጦር ከደመሰሰ በኋላ ወደ አፋፍ ወጥቶ በሰላምጌ ፤ በፉላ በሚያ
ጢቃበት ሰዓት እንዱ ጦርነቱ የሰለቸው ወይም የከበደው ወታ
ደር ፤ «ከምናልቅ እጃቸውን ይዘን ለእንግሊዝ እንስጣቸውና
እንገላገል» ቢል ፤ ጓደኞቹ «አንተ ዋሾ! ማነው እሳትን በእጁ
የሚጨብጥ» ብለው የተግሣጽ ጥያቄ ካቀረቡለት በኋላ ፤ «ደህና
ነው ፤ በል አንተ ለመያዝ ሞክርና እኛ በኋላ እናግዝሃለን» ብለው
አፌዘውበታል ።(2)

በውነትም በየጽሑፉ ላይ ዛሬ በንባብ ጠባያቸውን እንደ
ምንረዳው ፤ ቴዎድሮስ በፍጥረታቸው ከፖለቲካ ዘዴኛነት ፤
ከመልካምና ከታጋሽ አስተዳዳሪነት ይበልጥ የጦር ሥልት
ዐዋቂ ፤ በድፍረት ለመዋጋትም ፤ ለማዋጋትም ስጦታ ያላቸው
ጐበዝና ጦርጦራ የወታደር አለቃ ፤ በወታደር ዘንድ የሚፈሩ
የሚከበሩ ፤ የሚወደዱም ናቸው ። በቀውጢው የመጨረሻ ቀን
ብዙዎቹ ውጊያ የመረራቸው ቢሸሹም ብዙዎች መሸሸ ሲቻ
ላቸው ፤ «ሸሹ ፤ ፈቅጄላችኋለሁ» የሚል ቃል ከንጉሡ እንደ
በት ከሰሙ ወዲህ ፤ እምቢ ብለው ለርሳቸው ፍቅር ሲሉ እስከ
መጨረሻ በታማኝነት የተዋጉትን እናስታውሳለን ።

ዐፄ ቴዎድሮስ ፤ ይኸን ወታደራዊ ባሕርይ በፍጥረታቸው
ተጐናጽፈው የተወለዱ ስለሆነ ፤ ገና ከመዠመሪያው አነሣሣ
ቸው በትውልድ ወረዳቸው በቋራ ፤ በአውራጃቸው በደምቢያና
በመተማ ወሰን በሽፍትነታቸው ጊዜ ከቱርኮችና ከግብጾች
በመዋጋት ፤ ሰውነታቸውን ከጦርነትና ከችግር ጋር በደንብ አለ
ማምደውት ስለ ነበር ፤ ከዚያ ወዲህ የገጠሟቸው መሳፍንት
ሁሉ በፊታቸው ሊቆሙ አልቻሉም ።

1 Histoire de 1' Abysisonie A.M. Jones et Monroe pp. 177
2 አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 55

አስተዳደሩ በተበላሸው በራስ ዐሊ ቤተ መንግሥት በአማችነታቸው በመጠቀም በተድላ ፣ በደስታ ከመኖር ይልቅ በሽፍትነት በዱር ፣ በገደል በዐርበኝነት መቆየትን በመረጡበት ሰዓት የርሳቸውን አነሣሥ በቶሎ ለመቅጨት በየተራ የተላኩትን ደጃች ወንድይራድን ፣ ደጃች ጐሹን ራሳቸው ሳይታሰብ ቀጧቸው ። የራስ ዐሊ እናት ታላቂቱ እቴጌ መነን ሥፍር ቍጥር የሌለው ጦር ይዘው ፣ «ይኸ የፍየል እረኛ ፣ ቀለኛ አያመልጠንም» እያሉ በኩራት ወደቋራ ዘምተው ቢገጥሟቸው በትንሽ ጦር ካሣ የወደፊቱ ቴዎድሮስ ፣ ማርከው ጥሬ በማስፈጨት አዋርደው ፣ የፍየል እረኛ ተብለው የተሰደቡትን ተበቀሉ ።

ከዚሁ አከታትለው ባለፈው እንደ አነበብነው ሁሉ ፣ ራስ ዐሊንና ደጃች ውቤን ድል አድርገው ከነገሡና ሸዋን ፣ ወሎንና ትግሬን ከጠቀለሉ በኋላ ፣ አሁን በፍጥረታቸው ግዛትና ድል አድራጊነት የማይጠግቡ ስለሆኑ ፣ ኢትዮጵያን አዋሕደው ሳይጨርሱ የግዛት አሳባቸውን ከኢትዮጵያ ውጭ አደረጉ ። በአሳባቸው መካከል ያላቸውን መጠነኛ ጉልበት ከውጭዎቹ መንግሥታት ኃይል ጋር በደንብ አላመዛዘኑትም ።

የሆኖ ሆኖ ፣ ቴዎድሮስ በማናቸውም ረገድ በአገሪቱ የመከፋፈል ወቅት የተከፈለውን አገር ለመሰብሰብ የተነሡ ናቸው ። የራሳቸውን አገር አብስለው ሳያዋሕዱ ፣ የቱርክን የቄሣር ግዛት ለመቋቋምና ኢየሩሳሌምን ነጻ ለማድረግ መፈለጋቸውን ስናይ ጉልበታቸውንና ምኞታቸውን እንዳላመጣጠኑት እንገነዘባለን ። ባንድ ፊት አሠልጥኑኝ ብለው ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እንግሊዞችን ሲማጠኑ ፣ መልሰው ከእንግሊዞቹም ከፈረንሣዮቹም ሲጣሉ ፣ እነዚህ ኃያላን መንግሥታት በሥልጣኔም ፣ በኃይልም ከኔ ይበልጣሉ ብለው ከልብ አላመኑም ነበር ።

ከብዙ ዘመን ዠምሮ ፣ «በኢትዮጵያ ከወደ ምሥራቅ ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነሣና ዓለምን በዘንግ ይገዛል» የሚል ከቤተ ክህነት በኩል ሲነገር ነበር ። ስለዚህ የርሳቸውን አነሣሥና በመሳፍንት ላይ ተቀጣጥሎ የመጣውን አሸናፊነታቸውን የተመለከቱት ካህናት መነኮሳት ፣ «ትንቢት የተነገረልህ ንጉሥ አንተ ነህ» ብለዋቸዋል ።



እርሳቸውም በደረስጌ ማርያም በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው የነገሡለት ስመ መንግሥታቸው ቴዎድሮስ የተባለው ስለዚህ መሆኑን ባለፈው አንብበናል ። ከዚህ ጊዜ ቀጥሎ ሁሉንም ማንበርከክ ስለቻሉ ፣ የተነገረው ትንቢት የተፈጸመ ፣ ወደፊትም የሚፈጸም አድርገው ሳይወስዱት እንዳልቀረ ይገመታል ።

በመሳፍንት የሥልጣን ሽኩቻ ከውጭዎቹ የቅኝ አገር ፈላጊዎች ተጽዕኖና መሰናክል ጋር ሲደመር ፣ ከሰይፍ ጐን በሰላማዊ መንገድ የመምራቱ ጉዳይ ልዩ ስጦታ ይጠይቃል ። ቴዎድሮስ ቀደም ሲል ፣ በጦርነቱ ሁከት መካከል የባሪያን ንግድና አገዛዝ በማስቀረት ንግድ እንዲስፋፋ የነጋዴን የኬላ ጸጥታ የሚጠብቁ ወታደሮችን እየመለመሉ ፣ እንደ ፖሊስ በየበሩ በማስቀመጥ የጫካ ሽፍቶችን የመንገድ ቀማኞችን እየቀጡ በማጥፋት ፣ በየወረዳው ትክለኛ ባለጉልቶችን በተቻለ መጠን እየነቀሉ ለመንግሥታቸው ታማኝ የሆኑትን በመሾም ለየቤተ ክርስቲያኑ ቅዳሴ ብቻ ይበቃል ፤ ካህን ራሱን ጠምጥሞ በቤተ ክርስቲያን መቋሚያውን እያወዛወዘ ወገቡን እየሰበቀ (*) በዜማ ፣ በውዳሴ የሚያሳልፈው የማኅሌት ጊዜ ላገርና ለመንግሥት ምንም የተጨበጠ ዋጋ አለመስጠቱ ስለ ቆጫቸው ፣ የሰሞነኛውን ትተው የካህናቱን መሬት ወደ መንግሥት ወረሱ ። በዚህም ከፍ ያለ ጠብና ክርክር ከቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ጋር አብቅለው እንደ ነበር ይታወሳል ። ለዚህ የማሻሻል አስተያየታቸው ከጊዜው እንደ ቀደሙ ይታያል ።[1] ዳሩ ግን ፣ በሚያሳዝን አኳኋን የሾሙትን በጥርጣሬ በመሻርና በማሰር ፣ የሸፈተውን አገር በማዘረፍ ፣ ከውስጥም ከውጭም በተፈጠረ የጦርነት ጊዜ ሁሉም ውጥን እየመከነ ፣ በተለይ ወደ መጨረሻ ያለው ዘመናቸው በሁከት የተመላ ሆኖ እንኳን የሥልጣኔውና የልማቱ ዓላማ ግቡን ሊመታ ፣ በኃይል የሰበሰቡት አውራጃም ተመልሶ ተበትኗል ።

በማናቸውም ረገድ ፣ ይኸ ሁሉ ዐፄ ቴዎድሮስ ያደረጉት ውጣ ውረድ በመሠረቱ ለኢትዮጵያ አንድነትና ዕድገት ሲሉ

---

* ይህ አረግራጊ ፣ ራሱን ታጣቂ ፣ ወገቡን ሰባቂ ፣ አቴና ወጊ እያሉ ሰድበውታል ።

1 አለቃ ወልደ ማርያም ገጽ 27—28

መሆኑ አይጠረጠርም ። በዘመናቸው የጣሉት መሠረት አገር ጠቅሟል ። በመቅድሙ ላይ እንደ ጠቀስነው ፣ ደፋሩና ኃይለኛው ቴዎድሮስ በቅድሚያ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ በመከፋፈል በየ አውራጃቸው ሥር የሰደዱትን ባላባቶች በኃይል ነቅለው ያንድ ነቱን መሠረት ባይገነቡ ኖሮ ፣ ከርሳቸው ቀጥለው የነገሡት ዐፄ ዮሐንስ እና ዐፄ ምኒልክ ምቹ ያንድነት ጊዜ ወርሰው በመ ጠንከር ፣ በየዘመናቸው የተነሡባቸውን የግብጽንና የኢጣል ያን ወራሪነት በቀላሉ ለመመለስ ያዳግታቸው ነበር ። በዚህ ምክንያት የመከፋፈሉን ዘመን በኃይል አጥፍተው ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ለማቆም ያደረጉት ሙከራ በቀላሉ መገ መት እንደ ሌለበት እዚህ ላይ ማስተዋል እንችላለን ።

በማናቸውም ረገድ ፣ ለኢትዮጵያ ሲወጡ ሲወርዱ ቆይተው ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር በነበረ ቅራኔ ጦርነት ተጭሮ እጅግ ፈታኝ ሁኔታ ቢገጥማቸውም ፣ ቴዎድሮስ በጠላት እጅ ተማር ከው ራሳቸውንም ፣ አገራቸውንም ላለማዋረድ በአቋማቸው ጸን ተው ሕይወታቸውን ማሳለፋቸው የዠብዱ ሥራቸውን ያሳያል ። እስከ ሞት ድረስ የራሳቸውንም ክብር እንደ ምን መጠበቅ እንደሚወዱ ይኸው ራሱ ያስረዳል ። ስለዚህ ዛሬ በሕይወት ያለነው የኢትዮጵያን አንድነትና ዕድገት ከልብ የምንመኘው ሁሉ ፣ የቴዎድሮስን ድካምና መሥዋዕትነት በአክብሮትና በአ ድናቆት መዘከር እንዳለብን ደግመን እናስታውሳለን ።

ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለማሠልጠን የነበ ራቸው ሰፊ ዓላማ ፣ በጠላት ፊት ላለመዋረድ ራሳቸውን እስከ ማጥፋት የደረሱበት የቆራጥነት ታሪካቸው ፣ ባገር ላይ እንደ አጥቢያ ኮከብ በሰፊው በኢትዮጵያ ሕዋው ላይ እያበራ ጸዳሉ ያለማቋረጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሕያው ሆኖ ይተላለፋል ።

እንኳን እኛ ከዘመናቸው መቶ ዓመት ያህል ራቅ ብለን የምንገኘው ይቅርና ፣ በዚያው በዘመናቸው የነበሩት ኢትዮጵ ያውያን ያንድነቱን ትግል ያስከተለውን ፈተና በቀጥታ የተካ ፈሉት የግል ጉዳታቸውን ወደ ጐን አድርገው ፣ አባ ታጠቅ ቴዎድሮስ ቆራጥ ዠግና መሆናቸውን አድንቀው ለማስደነቅ ራሳቸውን ከገደሉ በኋላ ፣ እንደዚህ እያሉ በግጥም ያሞገሷቸው ወደ ጊዜያችን ደርሶ ሁልጊዜ ይነበባል ።



1. ስለ ዠግንነታቸው ፣

ሀ) በመቅደላ በኩል ጪኸት በረከተ ፤
የሴቱን አናውቅም ወንዳንድ (ወንድ አንድ)
ሰው ሞተ ።

ለ) ዳር እስከ ዳር ይዞ የገዛው ንጉሥ ፤
እንዲህን ስሱ ነው (እንደዚህ ስስታም ነውን)
ጠበንጃ እሚጐርስ ።

ሐ) ጠላቶቹን ሁሉ አጭዶ እንደ ገብስ ፤
መቅደላ ተጣለው ራሱን በራስ ።

መ) አባትና እናቱ አላንድ አልወለዱ ፤
አባ ታጠቅ ካሣ ያው አንዱ ፣ ያው አንዱ ።
(ያ ወንዱ ፣ ያ ወንዱ)

ሠ) የትግሬንም ንጉሥ ፣ የሸዋንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ፤
ወንድ አለራስዎ ገድለውም አያውቁ ።

ረ) አያችሁት ብያ (ወይ) ያንበሳውን ሞት ፤
በሰው እጅ መሞትን ነውር አድርጎት ።

ሰ) ገደልን እንዳይሉ ሙተው አገኙዋቸው ፤
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው ፤
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው ?
ለወሬ አይመቹም ተንኮለኛ ናቸው ።

2. በሥጋት ይመለከቷቸው ከነበሩ የተሠነዘሩ ግጥሞች ፣

ሀ) እምላክን መስሎ ቴዎድሮስ ፤
ንዑና ሑሩ (ኑ ሒዱ) ሲል ዋለ ሐሙስ ።
ሰኞ (የሞተበት ቀን ሰኞ) መቅደላ ተጨነቀ ፤
ሰው መሆኑ ታወቀ ።

## 3. የገኸርነት ፍላጐታቸውን ለመግለጽ

ሀ) ቀስ ብለሁ ግቡ ዝግ ብለሁ ግቡ ፣
ደሞ እዚያ ላይ (እሰማይ ቤት)
ወጥተሁ እንዳታስቸግሩ ፣
እኔው ብቻ ልግዛ ነውና ነገሩ ።

ለ) መላው የጐጃም ሰው ፣ መላው የትግሬ ሰው
ተይዞ በምጥ ፣
የእንግሊዝ ሐኪሞች መጥተው ቢይዙት ፣
ተገላገለ አሉ ይህ ሁሉ ፍጥረት ።(1)

ሐ) እሳት መጥቶ ተቋራ ፣
ድፍን አበሻን ሊበላ ፣
እንግሊዝ መጥቶ አጠፋው ፣
ለእግዚር እግዚር አለው ። (2)

---

1 ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ — አለቃ ወልደማርያም ገጽ 56—57 የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ. ኃ. ሥ. የመጨረሻ ዕትም ገጽ 39—40

2 Esercizi di Lettura Amarici
Raccolti da C. Conti-Rossini.......... pp. 1 - 19



# ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

### የመቀደላ ውድቀት ፣ ያፄ ቴዎድሮስ ሥርዓተ ቀብር ፣ የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ሞት ፣ የእንግሊዝ ጦር ወዳገሩ መመለስ

ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ሲገድሉ ፣ የመከላከሉ ጉዳይ አክትሞ የእንግሊዞች አሸናፊነት እስከ ዘለቄታው ተረጋገጠ ። የእርሳቸውም መሞት ሲታወቅ መቅደላ ታስሮ ከነበረው ውስጥ የቻለው በመቻኮል ከሰላምጌ የእንግሊዝ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ወደሚገኝበት ወደ እሮጌ ወርዶ ተደባለቀ ። በዚህ ምክንያት የመቅደላ ምሽግ ቤተ መንግሥቱ በዐሥር ሰዓት ተኩል ላይ በእንግሊዞች እጅ ወድቆ በብርጋዲዬር ጄኔራል ዊልቢ የሚመራው የእንግሊዝ ጦር በቁጥጥሩ ውስጥ ካስገባው በኋላ ፣ ዋናው አዛዥ ጄኔራል ሮበርት ናፒዬር በኢትዮጵያ መኳንንት ፣ በራሱ የጦር አለቆች እና በነሆርሙዝ ራሳም እንደ ታጀበ ማክሰኞ ሚያዝያ 7 ቀን ከእሮጌ ተነሥቶ ፣ በድል አድራጊነት ግርማ ወደ መቅደላ አፋፍ ወጥቶ የፋላንና የሰላምጌን ፣ የመቅደላንም ምሽግ ፣ የጦርነቱን ቦታ ሁሉ በጄኔራል ዊልቢ እየተመራ ጐበኘ ።

ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ አሟሟት ሁኔታውን በትክክል የሚመረምር ኮሚቴ የ33ኛ ሬጅሜንት አባል በሆነው በካፒቴን ጕህንስቶን የሚመራ ተቋቋሞ ፣ ኮሚቴው የዐፄ ቴዎድሮስን አሟሟት መርምረው የሚያረጋግጡ ሁለት ሐኪሞች ዶክተር ለሞሳዲን እና ዶክተር ብላንክን አዞ ነበርና ፣ እነዚህ ሁለት ሐኪሞች በራሳቸው ባፄ ቴዎድሮስ የልፍኝ አሽከር በወልደ ገቢርና በራሳም እየተመሩ ወዳፄ ቴዎድሮስ ሬሳ ሔደው ከመረመሩ በኋላ ፣ በእርግጥ ቴዎድሮስ በእጃቸው የገዛ ሽጉጣቸውን አፈሙዝ ባፋቸው ውስጥ ከተው በመተኮስ ራሳቸውን ገድለዋል ብለው በፊርማቸው አረጋገጡ ። ይኸው የሐኪሞቹ የምስክርነት ቃል በጽሑፍ ለዋናው አዛዥ ከቀረበለት በኋላ ፣ ዋናው አዛዥ ያፄ

ቴዎድሮስ ሬሳ እንዳገሩ ባህል ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሞ በደንብ እንዲቀበር አዘዘ ።

ለዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም በዋናው አዛዥ ፈቃድ ራሱ ሆርሙዝ ራሳም ተወከለ ። ራሳምም ምንም እስረ ኞቹን ለማስፈታት ከመጣ በኋላ ቴዎድሮስ ቢያስሩት ፣ በጭው ውት አሳብ ለአሳብ እየተለዋወጡ መስተንግዶው እንዳይጉ ድልበት አድርገው በመንከባከብ እንደ ግል ወዳጃቸው ይመ ለከቱት ስለ ነበረ ፣ ውክልናውን በደስታ ተቀብሎ የርሳቸውም የግል ቤተሰብ በዚህ በጦርነት ሰዓት ምንም ዐይነት መጉላላት እንዳይደርስበት አድርጓል ። ጠቅላይ አዛዡም ለንጉሣዊው ቤተሰብ አያያዝና እንክብካቤ ፣ ለቀብሩም ጉዳይ ከራሳም የሚቀርብለትን ጥያቄ በደስታ እየተቀበለ እንዲፈጸም ያደርግ ነበር ። ከራሳም ጋር ባለፈው በአስተርጓሚነትና በመላላክ ስሙን ደጋግመን ያነሣነው አቶ ሳሙኤል ጊዮርጊስ የሚባለው የሰናፌው ተወላጅ ፣ ወዲያና ወዲህ እያለ ያፄ ቴዎድሮስ አቀ ባበር በደንብ እንዲከናወን ፣ ሬሳው የሚለብሰውን ልብስ በማ ቀራረብ ከልብ መርዳቱን ራሳም ወዳገሩ ከገባ በኋላ በጻፈው መጽሐፉ ከምስጋና ጋር ገልጾታል ።(1)

ስለዚህ ዕጬጌ ገብረ ሥላሴ የንስሐ አባታቸው ፣ እስከ መጨረሻ ድረስ የሚወዱዋቸው ዘመዶችና አሽከሮች ባሉበት በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ። ከተቀበሩ በኋላ አንድ አዝማሪ እንደዚህ ብሎ ገጠመ ።

«ዐርባ ቀን (ሁዳዴ) ጦሞ ጦሞ ፋሲካ ሲደርስ ፤
ባፈር (በአፈር) ገደፈ (ፋሲካን ፈሰከ)
አሉ ያበሻ ንጉሥ» (2)

በዚህ ባፄ ቴዎድሮስ ቀብር ላይ ደንበኛዋ ባለቤታቸው የደጃዝማች ዓለማየሁ እናት እቴጌ ጥሩወርቅ ፣ ሌላዋም

1 Narrative of the British Mission.....Rassam P chap. XXVII pp. 329-343.

2 ፋዚላ....................ገጽ 49



የታወቁና የሚወዱዋቸው የየጁዋ ተወላጅ እቴጌ የተሙኙ የተገኙ አይመስልም ። በዚህ በግርግርና ያፄ ቴዎድሮስ ባላጋራዎች በተነሡባቸው ሰዓት ፣ በጠቅላይ አዛዡ ትእዛዝ ሕይወታቸውን ለመጠበቅ ኃላፊ እንዲሆን ኮሎኔል ሜርዌዘርን ልኮ ቤተሰቡን በሙሉ ከላይ ከሰላምጌ ምሽግ አስወርዶ እሮጌ አስቀምጧቸው ነበር ። በዚህ ጊዜ የቴዎድሮስ ወገን የሆነውን ሁሉ ለማጥቃት አጋጣሚ ጊዜ አግኝተናል በማለት የተነሡ ፣ ከሁሉ የበለጠ በወ ይዘሮ መስተዋትና በወይዘሮ ወርቂት የሚመሩት ባለፈው በቴ ዎድሮስ ጊዜ ጥቃት የደረሰባቸው የወሎ ተወላጆች ናቸው ። እነሱም በመቅደላ ያፄ ቴዎድሮስ የነበረውን ሁሉ ፈጅተው ያለፈ ቂጭታቸውን ለመወጣት ተዘጋጅተው ስለ ነበረ ፣ የእን ግሊዝ ባለሥልጣኖች ጥበቃውን በጣም አጠናክረውላቸው ነበር ። (1)

የሆነ ሆኖ ፣ ጄኔራል ናፒየር ማክሰኞ ወደ ምሽጉ ወጥቶ ከተረከበ በኋላ ፣ እዚያው እምሽጉም ለተገኘውና ቀደም ብሎ ወደ እሮጌ እየሸሸ ለመጣው ሁሉ ፣ እኛ በውስጥ ጉዳይ አንገባም የሚል ቃል ጨምሮ ሰፊ ንግግር አድርጎ ፣ መደምደሚያውን የእንግሊዝ መንግሥት በነጻ ለቋችኋል ብሎ ባስተርጓሚ ሲናገር ሕዝቡ ደስታና ዕልልታ አሰማ ። የዚህን ጉዳይ አለቃ ወልደ ማርያም በዚህ ዐይነት መዝግበውት ይገኛል ። « . . . ከዚህ በኋላ ሁሉም በሥልጣን (በእንግሊዝ ባለሥልጣን) እጅ ሆነ ። እንዲህ በሆነ ጊዜ ከሞት የተረፈ ከየሥራው እየመጣ በመቅደላ ቢሰበሰብ ሥልጣን የእንግሊዞቹ ሹም (ጄኔራል ናፒየር) ንጉ ሡን ከወደቁበት አስነሣ ለማስቀበር ። ቀኑም ማክሰኞ ማታ ነበረ ። የሞቱበት ግን ሰኞ ነው . . . በተቀበሩም ጊዜ መቃብር ሲደርስ እንደ በልግ ጊዜ በረዶ ቢዘንም ፣ ሰው ሁሉ በውሃ ጥም እጅግ ተጨንቆ ነበርና በረዶውን እያፈሰ ሲቅም ውሃ ጥሙ ታገሥለት ። ከየምንጩ የሚገኘውን ከየጉድጓዱም ባንድ ብር አንድ ዋንጫ ውሃ የእንግሊዝ ወገን እየገዛ ይጠጣ ነበር ። አለ ዋጋ ቀምተው የሚወስዱት ነገር ስለሌለ ።

በዚህም ጊዜ የምርኮውን ዙሪያ በመድፍና በነፍጥ አጥሮ ሦስት ዓላማ (ሰንደቅ ዓላማ) ነጭና ጥቁር ቀይ ተክለ . . .

1 Field - Marshal Lord Napier.....A Memoir by his son pp. 245.-246

የሐበሻ ሰው ምሬሃለሁ በየሀገርህ ግባ ብሎ ዐዋጅ ሲነገር ቋንቋው ባማርኛ ሲወጣ (ሲተረጐም) ዕልልታ ፣ ደስታ ተደረገ ።

በማግሥቱ ረቡዕ ሲረፍድ አንድ ሳይቀር የመቅደላ ሰው ወጥቶ ሰላምጌ ሠፈረ ። የእንግሊዞች ወገን ከአምባው ውስጥ (እመቅደላ ምሽግ) ገብቶ እስከ ዐርብ (ሚያዝያ 10 ቀን) ድንኳኑን ተክሎ ተቀመጠ. . . ከዚህም በኋላ. . . እነራስ ዳርጌ ፣ እነዋግሹም ተፈሪ ከእስራት ወጥተው ነበርና ከሥልጣን (ከናፒዬር) ቢገናኙ አባቶቻቸውን (ያባታቸውን አገር) ጠይቆ በየሀገራችሁ ግቡ አለ . . .»(*)

ስለ እንግሊዞች አመላለስ ወይም ከቴዎድሮስ ሞት በኋላ ስለሆነው ከአለቃ ወልደ ማርያም የበለጠ ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ እንደዚህ ይላሉ « . . . እንግሊዞች ገብተው ንጉሥ ወዴት ናቸው እያሉ ጠየቁ ። ከወደቁት (ከወደቁበት) ላይ አሳዩዋቸውና ደነገጡ ፤ አዘኑም ። ከዚያ ወዲያ የዕቃ ቤት የነበሩ ዕቃውን ፣ ቤቱን ያሳዩዋቸው ዝመሩ ። ነፍጡም ምንጣፉም መድፎችም(**) ከዚያ የቀዩ እስሮችም ተፈቱ. . . እቴጌ ጥሩ ወርቅም ከልጃቸው ከደጃች ዓለማየሁ ጋር ወደ እንግሊዝ ሠፈር ወረዱ ። እንግሊዞችም በክብረት (በክብር) ተቀብለው ምግባቸውን ይሰጡዋቸው ነበር ። . . . ይህን ካደረጉ በኋላ እንግሊዞች በመጡበት መንገድ ተመለሱ ።

ፈረሰኛም ፣ እግረኛም ባለመድፍም እንደ ሥራቱ አሰልፈው ፣ መኳንንቱም እንደ ክብረቱ ( እንደየማዕረጉ ) ልብሱን ለብሶ ሙዚቃ እየተነፋ ፣ የጦር አለቆቹ ጐራዴያቸውን መዘው ተሰለፉ ። ሎርድ ናፒዬርም በመካከል ነበሩ ። የርሳቸው ፈረስ ከፈረሶች ሁሉ ይረዝማል» እያሉ ጸሐፊው ከዘረዘሩ በኋላ ፣ ከዚሁ እያይዘው የእንግሊዙና የሕንዱ የእግረኛው ወታደር ባንድ ወገን ፣ ፈረሰኛው በሌላ ወገን እንደ ተሰለፈ በጥሩምባ እነፉፍና

* ገጽ 58—60 ወልደ ማርያም ራሳቸው እንደ ጠቆሙት ፣ ይኸን የታሪክ ማስታወሻ የጻፉት ቴዎድሮስ በሞቱ በ13ኛው ዓመት በ1873 ስለሆነ ዳርጌን ራስ ብለዋቸዋል እንጂ ፣ ሲፈቱ አቤቱ ዳርጌ ነው የሚባሉት ። ዋግሹም ተፈሪ የዋግሹም ወሰን ልጅ የዋግሹም ከበደ አባት ናቸው ። ለዋግሹም ጐበዜ የቅርብ ዘመድ ናቸው ።

** ነፍጡንም ምንጣፉንም. . .



በጦር መኮንኑ አዛዥነት ጠበንጃህን አውጣ ፣ ጠበንጃህን አውርድ እየተባለ ሰልፈኛው ከነመኳንንቱ ሥፍራ ሥፍራውን ከያዘ በኋላ የተጠንቀቅ ጥሩምባ ተነፍቶ ሁሉም ጸጥ ባለ ጊዜ ፣ አንድ የእንግሊዝ የጦር መኮንን ከፈረሱ ኮርቻ ላይ ቆሞ ባስተርጓሚ ለተሰበሰበው ሁሉ (በተለይ ለኢትዮጵያውያኑ) ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ዜጐችን አስረው አልፈታም ስላሉ ጦር ለመዝመት ተገዶ መምጣቱን ፣ የመጣውም ጦር አገር የማይዘርፍ ፣ ሰው የማይገድል የንግሥታቸው ጦር ሠራዊት ሁል ጊዜ አሸናፊ መሆኑን ገልጦ ለንግሥታችንና ለእንግሊዝ ሕዝብ ዕድሜና ጤና ይስጥልን ሲል ወታደሩ በጩኸት ሁራ ማለቱን ፤ . . . በነገታውም እንግሊዞቹ በባቤ ሜዳ ውሎ አድርገው ያዬ ቴዎድሮስ ወታደር የነበረውን ሁሉ እስረኛውንም በያገርህ ግባ ብለው ስንቅ እየሰጡ ማሰናበታቸውን ፤ እስረኛውም በየአገሩ መበታተኑን ይገልጻል ።(1)

የእንግሊዝ ጦር በመቅደላ ያገኘውን ብዙ የጦር መሣሪያ ፣ የቤተ መንግሥት ዕቃውንም ፣ አልባሳቱንም ፣ መጻሕፍቱንም ለራሱ በምርኮ ስም ወደ ሎንዶን ለመውሰድ ካከማቸ በኋላ ፣ ለመውሰድ ያልፈለገውን የሚረከበው ሁነኛ መሪ ፈልጎ ለመስጠት አስቦ ነበር ። ለጊዜው ከዋና ዋናዎቹ መሪዎች ደጃች በዝብዝ ካሣና ንጉሥ ምኒልክ በያገራቸው ተቀምጠዋል ። በአቅራቢያ የሚገኙት ዋግሹም ጐበዜ እምብዛም ራሳቸው ከእንግሊዝ ጦር ጋር መሰለፉን ስለ ጠሉት ወይም ስለ ፈሩት ፣ ለእንግሊዞቹ የዋድላውን ደጃች መሸሻን ተከተው እንግሊዝ ወዳገሩ ሲመለስ ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ከኔ አያልፍም ብለው በወገራና በወልቃኢት የሸፈተውን ጥርሶ ጐበዜን ለመደምሰስ ሔደዋል ። ስለዚህ የመቅደላን ምሽግ ለማስረከብ እንግሊዞቹ የዋግሹም ጐበዜን ወኪል ደጃች መሸሻን ቢጠይቁ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገለጡ ።(2) ደጃች መሸሻ ለመረከብ ያሠጋቸው ምናልባት በዙሪያ በቆቅ በርም ፣ በቃፊር በርም ያለውን የወሎዎችን ኃይል ሠግተው ይሆናል ።

መቅደላም የሚገኘው በወሎ ውስጥ ስለሆነ ፣ ወሎም በሁለት ዋና ዋና ባላባቶች ተከፍሎ ግማሹ በይማም ሊበን ልጅ

1 ቶዘላ ገጽ 49—52

2 Record of the Exp. Holland P. 76

በወይዘሮ ወርቂት ፣ ግማሹም በዐመዴ አባሙጃ ልጅ በወይዘሮ መስተዋት እየተመራ እነዚህ ሁለቱም እርስ በርሳቸው እየተጣሉ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ለጊዜው ቢቸገሩም ፣ የጦርነት ጠባይ ያለውን ምሽግ ካፈራረሱና በመቅደላ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ታጅሎ ከተቀመጠው ውስጥ ለመውሰድ የመደቡትን ያፄ ቴዎድሮስን ዘወዱን ፣ ማኅተሙንም ፣ ልብሳቸውንም ፣ መጻሕፍቱንም ፣ የጥንታዊ ነገሥታት እነ ዐፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ የሰጡትን የቁርባን ጥዋ ሳይቀር(*) ለይተው ከያዙ በኋላ ፣ የቀረውን ከዚህ በፊት እንዳነበብነው ፣ ከወርቂት ይበልጥ በአብደላ ዐሊ በኩል ቀረብ ብለው ለእንግሊዞቹ አገልግሎት ላበረከቱት ለወይዘሮ መስተዋትና ለወጣቱ ልጃቸው ለይማም ዐመዴ (አባ ዋጠው) ለሞግዚቱ ለአህመድ በሺር አስረክበው ፣ እስረኛውን በዐዋጅ በያገሩ እንዲገባ አሰናብተው በመጨረሻ ጦሩንና ምርኮውን ይዘው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በሚያዝያ 22 ቀን ወደ አገራቸው ለመመለስ ጉዞዋቸውን ዠመሩ ። የጉዞውም አቅጣጫ ያው መጥተውበት የነበረው በደላንታና በዋድላ በኩል የእንጣሎና ወደ ሰናፌ ወደ ዙላ የሚወስደው መሥመር ነው ።

ከጓዙም ነጠል ብለው ያፄ ቴዎድሮስ ደንበኛዋ ባለቤት እቴጌ ጥሩወርቅ(**) ከእናታቸው ፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸውና አገልጋዮቻቸው ጋር አብረው ይጓዛሉ ። የእቴጌይቱን መልክ ክሌሜንት ማርክሃም ከነዕድሜያቸው እንደዚህ ሲል መዝግቦት ይገኛል « . . . ዕድሜዋ ከ26 ዓመት አይበልጥም ። ከሚያምር ቅርፅና ጠጉር ጋር የተዋበች ቆንጆ ናት ። ከንፈሯ ሳሳ ያለ ነው ። ካንዲት የኢጣልያ ጠይም ሴት አትጠቁርም . . . »[1] ። ይኸው ጸሐፊና ወታደር ያለማየሁን ዕድሜ 10 ፣ የራስ መሸሻን ዕድሜ 20 ዓመት ያደርግና መሸሻ የተወለደው ከሕጋዊ ሚስት ስላልሆነ ፣ የቴዎድሮስ ደንበኛ ወራሹ ወጣቱ ዓለማየሁ ባሁኑ ጊዜ በራሳምና በኮሎኔል ሜርዌዘር ጠባቂነት ከናቱ ጋር በጉዞ ላይ መሆኑን ፤ መሸሻ ግን ፣ ከእሮጌው ጦርነት ወዲህ ቀደም

* በጥዋው ላይ ያለው ጽሑፍ «ዘንተ ጽዋዐ ዘወሀብዋ ዳግማዊ ኢያሱ ወብእሲቱ ወለተ ጊዮርጊስ ለቅድስት ቁስቋም ከመ ትኩኖሙ መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ» ይላል !!

** ከጋብቻው በፊት ጥሩነሽ ይባሉ የነበሩት.........

1 History of The Abyssinian Expedition Markham pp .361-362, Idem pp. 379-380).



ብሎ ወደ ሸዋ ሔዶ ከምኒልክ ጋር መደባለቁን ያመለክታል ።» መሸሻ ወደ ሸዋ ለመሔድ የወሰኑት ባንድ ወገን ምኒልክና መሸሻ ባፄ ቴዎድሮስ ቤት አብረው ያደጉ ጓደኞች ስለሆኑ ፣ በሌላ ወገን አሁን ያፄ ቴዎድሮስ ባላጋራ በበዛበት ወቅት ከቤገምድር ዘወር ብለው በሰላም ከምኒልክ ጋር በሸዋ ለመኖር ይመስላል ።

እቴጌይቱ ገና ከመቅደላ ዠምሮ ጤና አጥተው መሰንበታቸውን ናፒዬር በፖለቲካው መሪ በኮሎኔል ሜርዌዘር በኩል ሰምቶ ሐኪምም አዞ ቢታከሙም ፣ በዚህ የውጣ ውረድ ጉዞ አልተመቻቸውም ነበር ። ምንም ዐይነት እንክብካቤ ከኮሎኔሉም ፣ ከባልደረባቸው ከምስተር ራሳምም ቢደረግላቸው ፣ ከመንገዱ መጥፎነት በተጨማሪ ክረምቱም በመግባት ላይ ሆኖ ከላይ ዝናቡ ፣ ከታች ጭቃው የጉዞውን ችግር አባብሶት ስለ ነበር ፣ እቴጌይቱም ስለ ተዳከሙ ፣ ጉዞአቸው በቃሬዛ ላይ ተኝተው ነበር ። እቴጌይቱም ራሳም እንደሚለው በተፈጥሮአቸው ደርባባ ዝምተኛ ቢሆኑም(*) በዚህ ጊዜ ለማጽናናት ብሎ ፣ «አይዞዎት ፣ ይበርቱ ፤ ይድናሉ» ቢላቸው ፣ «እዬ እባክህ ለመሞት ቀኔ የተወሰነ ነው ። ብሞትም አላዝንም ። ጥንቱኑ ስፈጠር ከልጅነቴ ዠምሮ ለመከራ የተመደብሁ ነኝ ። አሁን መድኃኔ ዓለም ተስፋ ወደ ሰጠው ዓለም (መንግሥተ ሰማያት) ለመድረስ ብቻ ነው ምኞቴ» ብለው እንደ መለሱለት ያረጋግጣል ።[1]

እቴጌይቱ ለራሳም ፣ «ለመከራ የተፈጠርሁ ነኝ» ያሉበት ምክንያት በግልጽ እንደሚታወቀው ፣ አንደኛ ወላጅ አባታቸው ደጃች ውቤ ለመንገሥ በሚዘጋጁበት ጊዜ ፣ አሁን ባለቤታቸው በሆኑት በቴዎድሮስ በ1847 ዓ.ም. በጦር ተሸንፈውና በእስራት መጉላላት በዝቶባቸው ፣ «እኔን እንደዚህ ከማጉላላት ለኔ አንድ ጥይት አነሰኝ ?» እስከ ማለት ደርሰዋል ። በዚህ ዐይነት ከዐሥር ዓመት በላይ ታስረው ሲኖሩ በ1859 ዓ.ም. ዐረፉ ። ባለፈው እንዳነበብነው ፣ ያክስታቸው የወይዘሮ መንታዬ ልጆች ደጃች ንጉሤና ደጃች ተሰማ በ1852 ዓ.ም. ላይ በቴዎድሮስ ተሸንፈው በተማረኩ ጊዜ በሚያሰቅቅ አኳኋን ሲሞቱ ፣ እቴጌይቱ በወጣትነታቸው (18) ዓመት ከዚያው ከነደጃች ንጉሤ ሠፈር ተገኝተው ነው — ግዴታም ፣ ውዴታም ሆኖ ላፄ ቴዎድሮስ

* She was naturally taciturn and reserved.

1 Narrative PP. 344 - 348.

ሚስት ለመሆን የበቁት ። ወንድሞቻቸው ደጃች ጓንጉልና ደጃች ካሣ የተፈቱት ከመቅደላው ውድቀት በኋላ ነው ። በዚህም ላይ ያፄ ቴዎድሮስ ደንበኛ ሚስት በነበሩበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ የየጁዋን ቆንጆና ንግግር ዐዋቂዋን ወይዘሮ የተመኙን እንደ ሁለተኛ ሚስት አስቀምጠው ያስቀኑዋቸው ነበር ።

ስለዚህ ይኸ ሁሉ ሁኔታ ተጨማምሮ የጦርነቱንና የሁካታውን ጊዜ ለስላሳይቱና ቆንጆይቱ እቴጌ ጥሩወርቅ በጤንነት ሊሸከሙት አልቻሉም ። ቴዎድሮስ ራሳቸውን ከገደሉ በኋላም ፥ በቴዎድሮስ ያቄመው ሁሉ በስድብና በማስፈራራት እየተጋበዘ ለመዳን የቻሉት ፥ በእንግሊዝ የጦር መኰንኖች እርዳታና ጠባቂነት ነው ።([1]) በዚህ ሁሉ ምክንያት ለምለሙና ደካማ ሰውነታቸው በጦርነት ውዝዋዜ በበሽታ ተጠቅቶ አሁን ደግሞ በጉዞ ሰውነታቸው እየተዳከመ ሔዶ ትግራይ ሲደርሱ ፥ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ግንቦት 15 ቀን ዐርፈው በጄኔራል ናፒዬር ፈቃድ ሬሳቸው ወደ ሸለቆት ሔዶ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እናታቸውና ዘመድ አዝማድ እየተላቀሰ ፥ ደንበኛ ፍታትና ያቀባበር ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞላቸው በስመ ጥሩው የትግሬ መስፍን በራስ ወልደሥላሴ መቃብር ጐን በክብር ተቀበሩ ።(*)

ወንድሞቻቸው ጓንጉልና ካሣ ግን ፥ ገና አስቀድሞ አሸንጌ እንደ ደረሱ «እንግሊዞቹ እንዳደረጉ ያድርጓት» ብለው ተሰናብተው ወደ አገራቸው ወደ ስሜን ሔደዋል ። እናትዬዋና የቅርብ ዘመድ ግን ፥ እስከ ሸለቆት ደርሰው እቴጌይቱን አልቅሰው ቀብረው በተለይ እናትዬዋ ፥ ዓለማየሁ ያገሩን ያማርኛ ቋንቋ እንዳይረሳ አደራ በማለት ለእንግሊዞቹ ተማፅነው መሰናበታቸውን ራሳም ሲገልጽ የእናታቸውን ስም አልጠቀሰውም ።

ነገር ግን ፥ ሴትዬዋ እቴጌ ጥሩ ወርቅን ልጃቸውን ካጡ በኋላ ፥ ስለ ልጅ ልጃቸው ሕይወት ሥጋት ነበራቸውና ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ያደራ ደብዳቤ ላይ ስማቸው ላቂያዬ (ታላቂ) መሆኑና ስለ ልጅ ልጃቸው ያላቸውም ፍቅርና ሥጋት ከዚያ ላይ ይነበባል ። ቃሉም እነሆ «በስመ አብ. . . ከወይዘሮ ላቂያዬ የእቴጌ ጥሩ ወርቅ እናት ፥ የደጃዝማች ዓለማየሁ እሚታ

---

1 Hist. of The Exped. Markham p. 361 - 380.

* ራስ ወልደ ሥላሴ ትግራይን የገዙበት ዘመን ከ1782—1808 ዓ.ም. እንደ እ. ኤ. ቁ. 1790—1816 ። ሸለቆት የሚገኘው መቀሌ አጠገብ 18 ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ነው ።



(እያት) የተላከ ። ይድረስ ለንግሥት እንግሊዝ(*) ። እንባቢው እጅ ይንሣልኝ ፤ መድኃኔ ዓለም ጤና ይስጥልኝ ፤ መንግሥትዎን ያስፋ ፤ ጠላትዎን ያጥፋ ። ሦስት ደጃዝማቾች(**) እራተኛ እቴጌ (ጥሩ ወርቅ) ሞተውብኝ የቀረኝ ደጃዝማች ዓለማየሁ ነው ። አደራዎን ይጠብቁልኝ ። እግዚአብሔር አባቱንና እናቱን ቢነሣው እርስዎን ሰጥቶታል ። እኔም ካላየሁት ከሞቱት ቁጥር ነኝ ። እርስዎን እናቴ ይላል እንጂ እኔን እናቴ አይለኝም ፤ አላሳደግሁትምና ። እርስዎ ያሳድጉት ስለ እግዚአብሔር ብለው ።» ([1])

ራሳም በዚሁ መጽሐፉ ፥ «በኔው አመልካችነት አለቃ ዘነብ የሚባለው ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ክርስቲያን ያፄ ቴዎድሮስ የመዝገብ ቤት ኃላፊ የነበረው ፥ ላለማየሁ ሞግዚት ሆኖ አብሮት እንዲሔድ ከተፈቀደ በኋላ በየምክንያቱ አብሮት ሊሔድ አልቻለም» [2] ካለ በኋላ ፥ ዓለማየሁን ለፖለቲካው ሹም ለኮሎኔል ሜርዌዘር አስረክቦ እርሱ ወደ ክፍለ ሀገሩ መመለሱን ፤ በዚያም ሳለ መልዕክቱን ለመፈጸም ባደረገው ተጋድሎና በመቅደላና በሌላውም በደረሰበት ችግር ከፍ ያለ የምስጋና ደብዳቤ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ መቀበሉን ያስረዳል ። በመጨረሻ ግን ሉንዶን ከገባ በኋላ ፥ ለዓለማየሁ ሜርዌዘርም ቀርቶ ባለፈው ብዙ ጊዜ ስሙን ደጋግሙን ያነሣነው አበሾች ባሻ ፈለቀ የሚሉት ካፒቴን ስፒዲ በመንግሥት ፈቃድ ለዓለማየሁ ሞግዚቱ ሆኖ ንግሥት ቪክቶሪያም ከወይዘሮ ላቂያዬ በተጻፈላቸው ያደራ ደብዳቤ መሠረት በጀት መድበው ሲንከባከቡት ሳለ ፥ በአየሩም በምግቡም ለውጥ ጤና አጥቶ በመጨረሻ በ1879 ዓ. ም. እ.ኤ.ው አቆጣጠር ሞተ ።


---

* ለእንግሊዝ ንግሥት ለማለት ነው ።

** ሦስት ደጃዝማቾች የሚሉት ፥ ባለቤታቸውን ደጃች ውቤንና ከቴዎድሮስ ጋር ሲዋጉ የሞቱትን ወንድማማቾች ደጃች ንጉሤንና ደጃች ተሰማን ይመስላል ።

1 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ክፍል የሠነድ ፎ.ቁ. 739

2 አለቃ ዘነብ ከእንግሊዞች ጋር እስከ ግብጽ አገር ድረስ አብረው ከሔዱ በኋላ እንግሊዞች ወደ ምጥዋ መለሱዋቸው ። በዚያም ከእንግሊዝ ቆንሲል ከሙዚንገር ተገናኝተው ያፄ ቴዎድሮስን ታሪክ ሲያዘጋጁ ከርመው ቀጥሎ ከክራፍ ጋር መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ጋልኛና ወደ አማርኛ በመተርጐም አብረው ከሠሩ በኋላ ወደ አገራቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1876 ዓ.ም. ሞቱ ። (Evangelical Pionneers G. Aren pp. 446-448.)



የዐፄ ቴዎድሮስ ሰሎሞናዊ ኒሻን
(ከሪኮርድ ኦፍ ዘ ኤክስፔዲሽን ቱ አቢሲኒያ)



በምርኮ የሄደው የወርቅ ጽዋ
(ከዋሊስ ባጅ መጽሐፍ)



የእንግሊዝ ጦር በመልስ ጉዞ ላይ
(ከሮዜፔ አከቶን መጽሐፍ)



እቴጌ ጥሩወርቅና ነፃ የወጡት የትግሬ መኳንንት ከእንግሊዝ ጦር ጋር ወደ ትግሬ ሲጓዙ ።
(ከሮዝ አከቶን መጽሐፍ)



የእቴጌ ጥሩ ወርቅ ሬሣ ወደ ሸለቆት ለሥርዓተ ቀብር ሲጓዝ
(ከሮዤ አከቶን መጽሐፍ)



ዓለማየሁ ቴዎድሮስ በልጅነቱ
(ከሮገ፱ አክቶን መጽሐፍ)



የደጃዝማች ዓለማየሁ ሌላው ሐዘንተኛ ሥዕል
(ከሪኮርድ ኦፍ ዘ ኤክስፔዲሽን ቱ አቢሲኒያ)



ደጃዝማች ዓለማየሁ በእንግሊዝ አገር
(ከዶክተር ብላንክ መጽሐፍ)



ደጃዝማች ካሣ ምርጫ ጄኔራል ናፒዬርን ሲሸኙ
(ከሮጀር አክቶን መጽሐፍ)

# ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

## የናፒዬር ለሽናፊነት በሎንደን ስለ መሰማቱና የተደረገለት አቀባበል

በእንግሊዝ አገር በተለይ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ቢሮ (ዳውኒንግ ስትሪት)፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ቢሮ፣ በሕንድ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አካባቢና በቦምቤይ፣ በኤደንና በመካከለኛው ምሥራቅ ሁሉ ያፄ ቴዎድሮስ ስም ባንድ ወገን በሀገራቸው ውስጥ ስለሚፈጽሙት ተግባር፣ ወዲያውም በቱርኮችና በግብጾች ላይ ያላቸው የተቃውሞ መንፈስ፣ በሌላው ወገን በጦርነት ያወጋግ ዝብዷቸውና አሸናፊነታቸው ከየመንገደኛው፣ ከየንግድ ወኪሉ አንደበት ወይም ጽሑፍ እየተነገረ ገንኖ ይወራ ነበር።

የእንግሊዝ መንግሥት የራሱን ዜጎች ብቻ ሳይሆን፣ የቀሩትንም የአውሮፓውያን እስረኞች ሕይወት አደጋ ላይ ላለመጣል ቸኩሎ በጦርነት ላለመጋፈጥ ያደረገውን ጥረት ባለፈው አንብበናል። አሁን ደግሞ፣ በግዴታ የዘመቻው ጉዳይ በምክር ቤት (ዌስት ሚኒስቴር) ሲወሰን፣ ምንም እንኳን በጦርነቱ ዋዜማ ባሉት የሁለትና የሦስት ዓመታት ጊዜ ቴዎድሮስ በዘጌ፣ በደምቢያ፣ በጐንደር፣ በደብረ ታቦርና በዋድላ ባካሔዱት ዘመቻ ምክንያት ብዙ መኳንንት እንደ ከዷቸው፤ የገዛ ወታደራቸውም ጦርነት እንደ ሰለቸው ከውስጥ ዐወቅ ሰላዮቻቸው ከነአክበር ዐሊ እየተገናዘቡት ለዘመቻቸው አመቺ ሁኔታ መፈጠሩን ቢረዱትም፣ እንግሊዞች እንደዚህ ባጭሩ ጦርነቱ እንደሚፈጸም በቅድሚያ ስለ አልገመቱ፣ ዘመቻውን ያዘጋጁት በጥንቃቄና በከፍተኛ ወጭ ነበር።

ለዚህ ዘመቻ የእንግሊዝ መንግሥት ወጭ ያደረገው እንደ ዋልዳማዩር አባባል፣ 10,000,000 ፓውንድ ስተርሊን ነው። ነገር ግን፣ እንግሊዞቹ ራሳቸው የተመኑት 8,900,000 ስተርሊን

ነው ። ([1]) ይኸም በዚያን ዘመን የኤኮኖሚ አቅዋም ከፍተኛ ወጭ ነው ። በዛሬው የኢትዮጵያ ምንዛሪ አንዱን ስተርሊን ከሰባት ብር ላይ ብናቆመው ፣ 8,900,000 x 7 ...... 62,300,000 የኢትዮጵያ ብር ይሆናል ። የዚህንም አጋማሹን የፈጀው የባሕሩ ላይ ማጓጓዣ ነው ። ግመሉ ፣ በቅሎውና ዝሆኑ በየብስ ላይ ከዙላ እስከ መቅደላ ያጓጓዘው ሁሉ አስቀድሞ በባሕር ላይ ተጉዞ ነው ።

በተለይ በዚሁ በጦርነቱ ዝግጅት መካከል ፣ በእንግሊዝ ባለሥልጣኖቹ ዘንድ ንጉሥ ቴዎድሮስ በራሳቸው ሕዝብ ላይ እንደዚያ የማያወላውል ርምጃ የሚወስዱት ፣ ለዚህ ጦርነት መሠረታዊ ሰበብ የሆኑትን በእጃቸው የታሰሩትን የውጭ አገር ዜጎች በሕይወት የማሰናበታቸውና ወይም የመፍጀታቸው ጉዳይ በየባለሥልጣኖቹና በየቤተሰቡ ሕሊና እየተንቀዋለለ ፍቺ ያጣ እንቆቅልሽ ሆኖ የመንፈስ ዕረፍት ነሥቶ ነበር ። የንጉሡን ልብ ለማራራት ይረዳል ተብሎ ፣ የእስረኞቹ ቤተሰቦች በቀጥታ የልመና ደብዳቤ እንዲጽፉላቸው የተደረገውም የማስለቀቂያ አንድ ዘዴ ይሆናል ተብሎ ነበር ።

አሁን ግን ፣ ጄኔራል ናፒዬር ያለብዙ መሥዋዕት የተሠጋበትን ውጊያ ማሸነፉን ፣ እስረኞቹን በሕይወት መረከቡን ፣ የቴዎድሮስን ሞት ጭምር በዚያው በሞቱበት ቀን ፣ ዕለቱን በቴሌግራም ከመቅደላ አስታውቆ ስለ ነበረ ፣ በጭንቀቱና በሥጋቱ ፈንታ በሎንዶንና በቦምቤይ ታላቅ ፍ/ ሐና ደስታ ተተካ ።

በሰፊው እንዳነበብነው ፣ ጄኔራል ናፒዬር ከመቅደላ ወደ መጣበት ወደ ዙላ ወደብ ከመመለሱ በፊት ፣ የራሱን የጦር አለቆች የእንግሊዙንና የሕንዱን ተዋጊ ሠራዊት በባቤ ሜዳ ላይ ሞቅ ባለ ዲስኩር ልባዊ ምስጋና አቅርቦ ፣ ጉዞውን በዋድላ ደላንታና በአሸንጌ በኩል አድርጎ እንጣሎ በደረሰ ጊዜ ከእንግሊዝ ንግሥትና ከየባለሥልጣኖቹ ፣ «እንኳን ቀናህ» የሚል የቴሌግራም ቃል ከደረሰው ወዲህ ፣ አሁን ከመቅደላ ዠምሮ ባልተለዩት በእንደርታው ባላባት በባልጋዳ አርአያ (በኋላ ራስ) በአጋሜው ባላባት በአረጋዊ ሰባጋዲስ (በኋላ ዋግሹም) በየመንገዱ

1 Letters of Field - Marshal Lord Napier.........P. 23.



በሚያገኛቸው መኳንንት እንደ ታጀበ እንጣሎን ዐልፎ በግንቦት 25 ቀን ሰናፌ (አከለ ጉዛይ) ገባ ።

በዚያም በፊተኛው ጊዜ ሲመጣ በወዳጅነት ተቀብለው ያስተናገዱት ደጃች ካሣ ምርጫ (በኋላ ዐፄ ዮሐንስ) በጦር ሠራዊታቸውና በመኳንንቶቻቸው ታጅበው ፣ ደግሰው መልካም የክብር አቀባበልና መስተንግዶ አደረጉለት ። እርሱም የተከተሉትን እነ ባልጋዳ አርአያን ለደጃች ካሣ እንደ ባላንጣ ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉ ከካሣ ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ ፤ ራሳቸውን ካሣንም ከዋግ ሹም ጎበዜ ጋር መዋጋት እንዲተዉ ሐሳቡን ካሰማ በኋላ ፣ አሁንም በፊተኛውም ጊዜ ላደረጉት መስተንግዶና እርዳታ በበኩሉ ላንድ ሬጅሜንት በቂ የሆነ የጦር መሣሪያ ፣ 12 መድፍና ብዙ ጠበንጃ ከነጥይቱ ሰጣቸው ።

እዚሁም ሳለ ፣ በእንጣሎ ከደረሰው ከንግሥቲቱና ካለቆቹ አጭጭር ቴሌግራም በተጨማሪ አሁን ረዘም ያለ ደብዳቤ ከውጭ ጉዳይና ከመከላከያ ሚኒስትሮች ፣ ከሕንድ አገረ ገዥዎች በጉዞው ላይ ይደርሰው ዠመር ። ከመከላከያው ሚኒስቴር ከሎርድ ዦርዥ የመጣለት ደብዳቤ እንደዚህ የሚሉ ቃላት ይገኙባቸዋል ። «. . . እሑድ ለት ስለ መቅደላ ውድቀት የላኩብኝ ቴሌግራም በደረሰኝ ጊዜ የተሰማኝን ደስታ የምገልጽበት ቃል አላገኘም ። በእርስዎ ከፍተኛ ጥረትና በብልህነትዎ በሚመራው የእንግሊዝና የሕንድ ወታደሮች ድካም ፣ ይህ አስደሳች ውጤት ስለ ተገኘ ፣ እንኳን ደስ ያለዎት እያልሁ ልባዊ ስሜቴን እገልጻለሁ ።»

ሚኒስትሩ ደብዳቤያቸውን በነዚህ ቃላት ከዠመሩ በኋላ ፣ ስለ ራሳቸው ስላዔ ቴዎድሮስ አሟሟት እንደዚህ ብለዋል ። « . . . በመቅደላ የወራራ ሰዓት የቴዎድሮስ ሞት እርስዎን ካንድ ግራ አጋቢ ሁኔታ ገላግሎዎታል»(*) ። የሚኒስትሩ አባባል ቴዎድሮስ በሕይወት ቢማረኩ ኖሮ ፣ ይታሰሩ ወይስ ይገደሉ አለዚያስ ወደ ኢንግላንድ ተወስደው በግዞት ይኑሩ ወይስ ይለቀቁ የሚል አወዛጋቢ ሁኔታ ከሚፈጥሩ እንኳን ሞቱ የሚል ይመስላል ።

* በትክክል የእንግሊዝኛው ቃል «The Death of the Theodore during the assualt has relieved you of a great embarrassment»

የመከላከያ ሚኒስትሩ ስለ እስረኞቹ መለቀቅ ሲያወሱ ፤ «የእስረኞቹ በሕይወት መለቀቅ ትልቁ የምኞታችን ዓላማ መልካም ፍጻሜ አገኘ» ካሉ በኋላ ፤ ስለ ራሱ ስለ ናፒዩር ልዩ ችሎታ «. . . የዘማቹ ጦር አመራር መልካም ውጤት ያገኘ ዘንድ አገራቱ እርስዎን የመሰለ ጄኔራል በማግኘቷ ታድላለች ብል ቃለ አጋኖ አይሆንም . . . የዘመቻውን ዝርዝር ውጤት ለማንበብ በጕጕትና በችኰላ እጠባበቃለሁ ። እርስዎም ወደኛ እንደሚመለሱና ጠቅላላውም ጦር በግንቦት ወር መጨረሻ አበሻን ለቆ እንዲወጣ ተስፋ አደርጋለሁ ። በሐቅ ታማኝዎ ጕርኸር» በማለት ይደመድማሉ ።(1)

ናፒዩር ከመቅደላ ከተነሣ ወዲህ ፤ በየመንገዱ ይኸን የመሳሰሉ ቃላት ከያለበት እየደረሰው በሰናፌም ከደጃች ካሣ ጋር በወዳጅነት ሲወያይ ሲመካከር ከሰነበተ በኋላ ፤ በዚህ ዘመቻ መንገድ በመምራት ፤ በአስተርጓሚነት ላገለገሉት ለነምርጫ ወርቄም ፤ ለሌሎቹም እንደ ደረጃቸው የመሣሪያም ፤ የዕቃም ፤ የጥሬ ገንዘብም ስጦታ አድሎ ሲጨርስ እንደ .ኤ.አ. በግንቦት 29 ቀን ከነጦሩ ከሰናፌ ተነሥቶ በሰኔ 10 ቀን ዙላ ወደብ ገባ ። በዚያም በምጥዋ የግብጾቹ ገዥ አብዱል ቃድር ባሻ መጥቶ ተገናኘው ።

ከዚህ በኋላ ፤ እንደ በላዮቹ ትእዛዝ ዋናውን የእንግሊዝንና የሕንድን ጦር ወደ መጣበት ወደ ቦምቤይ (ሕንድ) ልኮ እርሱ ዋና ዋናቹን የጦር መኳንንት እንዳስከተለ በስዌዝ ዐልፎ በሰኔ ወር ወደ መጨረሻው ለንደን ገባ ። ብዙ የጦርና የፖለቲካ ባለሥልጣናት ከብዙ ሕዝብ ጋር በደስታ የክብር አቀባበል አደረጉለት ። በፓኪንግሃም ቤተ መንግሥት ፤ በዳውኒንግ ስትሪት ፤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኒዩቨርሲቲም ሁሉ የምስጋና ዲስኩር ለርሱና ለጓደኞቹ ጭምር እየተደረገ ፤ ከዚያም በለንደን ምክር ቤት ልዩ ጊዜ ተወስኖ በስብሰባ ፤ በጭብጨባና በሆታ ተቀብለውት የወደፊት የጡረታ ያመት ደመወዙ 2,000 ስተርሊን እንዲሆን በምክር ቤት ተወሰነ ። ቀጥሎም ባሮን ኦፍ መቅደላ

1 Letters of Field-Marshal Lord Napier.........pp. 18-19



ተብሎ ትንሽ እንደ ቆየ በራሱ ጥያቄ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በዲስራኤሊ አቅራቢነት በንግሥቲቱ ፈቃድ ከልዩ የኒሻን ሽልማት ጋር ሎርድ ናፒዩር ኦፍ መቅደላ የሚል ሥያሜ ተሰጠው ።(1)

ከርሱም ጋር ለዘመቱት ለ2 አዛዦች ፤ ለ27 የኮምፓኝ አዛዦች ፤ ለ15 ኮሎኔሎች ፤ ለ18 ሌተና ኮሎኔሎች ፤ ለ30 ማዦሮች የኒሻን ሽልማትና የሹመት ዕድገትም ተሰጣቸው ። በተለይ ኮሎኔል ዊልያም ሜርዌዘር በኤደን ከተማ የነበረውን የውክልና ደንበኛነት ሥራውን ትቶ ፤ በዚህ የመቅደላ ዘመቻ ጊዜ በፖለቲካ ኃላፊነት በትጋት መሥራቱ ታውቆለት የብሪጋዲዩር ጄኔራልነት ማዕርግና ኮማንደር ኦፍ ዘስታር ኦፍ ኢንዲያ የሚባል ኒሻን ተጨምሮ ተሰጠው ።(2)

ጄኔራል ናፒዩር ፤ ምንም እንኳ በዚህ ጊዜ (1868 እ.ኤ.አ) ዕድሜው ወደ 58 ዓመት ቢሆን ፤ ወደ ጡረታ ሳይገለል ከ1870 እስከ 1876 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በሕንድ የእንግሊዝ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ቆይቷል ። በ1882 ዓ.ም. ላይ ፊልድ ማርሻል ተብሎ በጅብራልታር (1876 - 1882) ዋና አዛዥ ሆኗል ። ከ1882 እስከ 1890 ዓ.ም. ድረስ በምክር ቤትም ፤ በሌላውም ፤ በኢትዮጵያም በሕንድና በቻይና ጉዳይ በሁሉም ዘንድ ተጠያቂና የክብር አማካሪ ሆኖ ሲኖር ፤ በእንፍሉይንዛ በሽታ ታሞ ባጭር ጊዜ ውስጥ እ.ኤ.አ. በ1890 ዓ.ም. በሰማንያ ዓመቱ ሞቶ በክብር ተቀበረ ።(3)

1 Field-Marshal Lord Napier of Macdala, A Memoir by his son..... 1. 232-254, 315-319.

2 Letters of Field-Marshal Lord Napier - p. 19. History of the Abyss. Exp. Markham - pp. 355-391

3 Exped. to Abys. Holland Vol. II Chap. XX-XXV, XXXVII Narrative - H. Rassam Chaps, XXVI-XXVII. Ten years with King Theodore - Th. Waldmeir - Chap. XI-pp. 121-129.

## ምዕራፍ ዐርባ

### እንግሊዝ ከኢትዮጵያ ለቀ የወጣበት ምክንያት

በ19ነኛው ምዕተ ዓመት ላይ ዋና የቅኝ አገዛዝ ፉክክር በጀርመን ፥ በቤልዥክ ፥ በሆላንድ ፥ በፈረንሣይና በእንግሊዝ መካከል በሚፋፋምበት ጊዜ ፥ በሌላው ክፍለ አህጉር ብዙ ጊዜ ከመንግሥታቸው ትእዛዝ ውጭ ባገር ተወላጅ ሕዝብ ላይ ብዙ የማጥቃት ሥራ የሚፈጽሙት የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች በዚህ በመቅደላ ጦርነት ያሳዩት አቅዋም ለየት ያለ መልክ ነበረው ።

ከቶውንም ፥ የቅኝ ገዥ ርኅሩኅና መብት ጠባቂ በዓለም ላይ እንደሌለ ግልጽ ነው ። እንግሊዞችም እንደ ሌላው በእስያ ፥ በአፍሪካና በደቡብ አሜሪካ ዐልፎ ዐልፎ ያደረጉት ጭካኔ ፥ ወገንንም ለመከፋፈልና የነርሱን አገዛዝ ለማጠናከር የሚያደ ርጉት ዘዴ በየመጽሐፉ ተመልክቷል ።

ኢትዮጵያ ከ1928 እስከ 1932 ዓ. ም. ድረስ በኢጣልያ የፋሺስት መንግሥት በተወረረችበት ሰዓት ፥ ለኢትዮጵያ ነጻ መውጣት ምክንያት የፈጠረውን ጦርነት አዶልፍ ሒትለር በአውሮፓ በ1931 ዓ. ም. ቢቀሰቅስና የእንግሊዝና የፈረንሣይ መንግሥታት ወደ ሒትለር እንዳይደረብ ቢያባብሉት ሙሶሊኒ የሒትለር ጊዜያዊ ኃይል የሚያዋጣ ፥ የፈረንሣይም ወድቀት ለዘለቄታ መስሎት ለመሬት ክፍያ በመጓጓት የእንግሊዞችን ማባበል እምቢ ብሎ በሒትለር ጐን ተሰለፈ ።

በዚህ ጊዜ ፥ ኢትዮጵያ በተወረረችበት ሰዓት እርዳታ ከነፈ ጉን ውስጥ አንደኛው የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ፥ ጠላታ ችን ኢጣልያ የነርሱም ጠላት መሆኗን ሲያረጋግጡ ፥ እንግሊዞች የኛ ረዳት ሆነው በስደት የነበሩትን የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ወደ ካርቱም አ͡መጡ ። ነገር ግን ፥ ከሎንደን ወደ ካርቱም ሲነሡ

አንዳንድ ባለሥልጣኖች ኢጣልያ ኢትዮጵያን ቢለቅ በኢጣልያ እግር ለመተካት አምሯቸው የንጉሡን ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ መምጣት በመቃወም ብዙ እንቅፋት ፈጥረው እንደ ነበረ የሚታወስ ነው ።

ነገር ግን ፣ በእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ዘንድ ከፊሉ ኢትዮጵያን ቅኝ ለማድረግ ሲያሤር ፣ በዚያው ጐን የኢትዮጵያን ነጻነት የሚደግፉ አልጠፉም ። ስለዚህ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነአንቶኒ ኤደን ደጋፊነትና በብዙ ጥረት ወደ ካርቱም ከገቡ በኋላ ፣ ዐርበኛውና ስደተኛው ከመሪው ጋር ተገናኝቶ እንዳይተባበር ፣ መሪውም እንደ ግማሽ እስረኛ ሆነው እንዲቆዩ የእንግሊዝ ጦር የኢጣሊያን ጦር ካስወጣ በኋላ ፣ ለአገሪቱ ሲዋጉ ለቆዩት ዐርበኞችና ከርሱው ጦር ጋር አብረው ለመጡት ስደተኞች በማስረከብ ፈንታ ፣ «በወታደርነት የተያዘ የጠላት መሬት አስተዳደር» በሚል ሥያሜ በእንግሊዝ እጅ እንደ ተያዘች እንድትቆይ ፤ ከዚያ በኋላ ሁኔታው እየታየ ኢትዮጵያ የአማራ ፣ የጋላ ፣ የትግሬ ተብለው በታናናሽ መሳፍንት ተከፋፍላ እንድትተዳደር ፣ የደቡብም የሲዳሞና የገሙጐፋ አካባቢ ወደ ኬንያ፣ወደ ውጋንዳ እንዲዋሐድና በቀጥታ የእንግሊዝ ቅኝ አገር እንዲሆኑ ታቀደ ። ይኸንንም የሚያውጠነጥኑ የውጋንዳው ገዥ ሰር ፊሊፕ ሚቸል እና የሱዳን አስተዳዳሪ የነበረው ዠኔራል ላሽ ነበሩ ።

በዚህ ዐይነት ፣ ኢትዮጵያ ተከፋፍላ በእንግሊዝ ሥር ስትሆን ራሱ ፊሊፕ ሚቸል በኢትዮጵያ የእንግሊዝ እንደራሴ ለመሆን ጽኑ ፍላጐት ነበረው ። የርሱንም አሳብ ቅኝ አገር የጣማቸው የእንግሊዝ ዤኔራሎች እነ ዊሊየም ፕላት ጦርነቱን የተካፈሉት የደቡብ አፍሪካ መሪዎች ተቀብለውት ነበር ።

ነገር ግን ፣ እላይ እንዳልነው በእንክርዳዶች መካከል ስንዴዎች እንደሚገኙ ፣ ከላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አንቶኒ ኤደን ከታች ወደ ኢትዮጵያ ለዘመተው ጦር የክፍል አዝማቾች የነበሩት እነ ኮሎኔል ሳንድፎርድ ፣ እነ ኮሎኔል ዊንጌት የከፋዎቹን አሳብ በመቃወም ፣ ኢትዮጵያን የመገንጣጠሉም በቅኝነት የመግዛቱም ጉዳይ እያደር እየሳተ ሲሔድ ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አምስት ዓመት በውጭ አገር የኖረውም ስደተኛ በተለይ ካገሩ ሳይነቃነቅ በነራስ አበበ መሪነት የተዋጉት ዐርበኞች አዲስ አበባ



ከእንግሊዝ ጦር በፊት ቀድመው እንዳይገቡ በእንግሊዝ ባለሥልጣኖች በኩል የተወሰነው የማስፈራሪያ ውሳኔና የድል ሽሚያ ሌላውን የእንግሊዝን የአቅኝነት (የቅኝ ገዥነት) መንፈስ አጉልቶ የሚያሳይ ነበር ።

ምንም እንኳን ፣ አዲስ አበባ ያሉት የኢጣልያ ሹማምንት ኢትዮጵያውያን ቀድመው ከገቡ ያለፈውን ፣ የሠራነውን ግፍ እንበቀላለን ማለታቸው አይቀርምና እንዋጋለን ። የእንግሊዝ የጦር አለቆች ግን ፣ ቀድመው አዲስ አበባ ከገቡ በሰላም እጃችንን እንሰጣለን ብለው ማመልከታቸው ባይዘነጋ ንብረት ለመሸማቱም ፣ ሥልጣን በቅድሚያ ለመጨበጡም ቢሆን ፣ እንግሊዞቹ አዲስ አበባን ቀድመው ለመያዝ የራሳቸው መሠረታዊ አሳብ እንደ ነበረ አይሰወርም ።

የሆነ ሆኖ ፣ የዚህን ሁሉ የእንግሊዞችን የፖለቲካ ተንኮል ያልተገነዘብነውና ነጻነት የናፈቀን የዚያን ጊዜ ወጣቶች ፣ የእንግሊዝ ጦር የኢጣልያንን ጦር በሰሜንና በደቡብ ደምስሶ አዲስ አበባ የገባለት እንደ ነጻ አውጭ ጦር በመቁጠር በደስታ ተቀብለነው ነበር ። እያንዳንዱ የእንግሊዝ መኰንን ወይም ወታደር በከተማ ሲዘዋወር ፣ እንደ አንድ አዳኝ መልአክ በመቁጠር በፈገግታ እንመለከተው ነበር ።

ነገር ግን ፣ ከእንግሊዞች አገባብ ተከታትሎ ስደተኛውም ፣ ዐርበኛውም አዲስ አበባ ገብቶ የኢትዮጵያ ባንዲራ በአዲስ የሥነ ሥርዓት በዓል ተሰቅሎ ፣ የኢትዮጵያ ነጻነት እንደ ምንም እየተረጋገጠ በሚሔድበት ጊዜ ፣ ባንድ ወገን እኛ በገባንበት ቡና ቤት ኢትዮጵያውያን አይገቡም እያሉ አምባጓሮ ሲያነሡ ፣ ኢጣሊያኖች በኢትዮጵያ የዘረጉትን ማናቸውንም የፋብሪካና የመሣሪያ ዕቃ እየነቃቀሉና እየዘረፉ በመውሰድ ፣ ለመውሰድ ያቃታቸውን ለኢትዮጵያ ቀርቶ እንዳያገለግል ማፈራረሳቸውን ስንመለከት ፣ በእንግሊዞች ላይ የነበረንን መልካም ስሜት በሚያሳዝን አኳኋን እነሱው ራሳቸው መልሰው አፈረሱብን ። ([1])

1 The Negus - L. Mosley - ከኢጣልያንኛው ትርጒም (በራሴ) ገጽ 328—336 ፣ 344—351 ፣ 352—369

ከዚሁ ጋር የነበራቸው መሠረታዊ ዓላማ ፣ ኢትዮጵያን
አዳክሞ ለመግዛት ስለ ነበረ ፣ በኢጣልያኖች እጅ የነበረውንም ፣
በየመጋዘኑ የታጀለውንም ልዩ ልዩ ዕቃና የጦር መሣሪያ በኢት
ዮጵያውያን እጅ እንዳይገባ በሽሚያ እየሰበሰቡ መውሰዱ በጊ
ዜው የጦርነት ሰዓት ስለ አዳገታቸው ፣ ከያለበት በካሚዎን
እየሰበሰቡ ወደ አባ ሳሙኤልና ወደ ቢሾፍቱ ሐይቅ በማጋዝና
በመጨመር ፣ ባሕር በልቶት እንዲቀር ማድረጋቸው ታሪኩ የቅ
ርብ ጊዜ ስለሆነ አይዘነጋንም ። በሕይወት ያሉትና በጡረታ
ላይ የሚገኙት የብሪታንያ ወታደሮችና ሹማምንቶችም በትዝታ
ሊያስታውሱት ይችላሉ ።

አንዳንድ እንግሊዞች ፣ እንደዚህ ያለውን የከፋት ሥራ የሠ
ሩት የደቡብ አፍሪካ ወታደሮች ናቸው የሚል ምክንያት ይሰ
ጣሉ ። ነገር ግን ፣ እነርሱንም በበላይ የሚመሩዋቸው የእንግሊዝ
ባለሥልጣኖች የመከፋፈሉንም መሣሪያ ፣ የማፈራረሱንም ተን
ኰል ያመነጩ ራሳቸው እንግሊዞቹ ስለሆኑ ፣ እንደ ጲላጦስ በነ
ገሩ የለንበትም ብለው እጃቸውን ታጥበው ንጹሕ ለመሆን
አይችሉም ።

ይኸ ሁሉ አድራጐት ፣ አንድ ግራ አጋቢ የሆነ ነገር ያመለ
ክታል ። የቅኝ ግዛት በተፋፋመበት በ19ነኛው መቶ ዓመት
አጋማሽ ላይ ቴዎድሮስን ከመቅደላ ላይ ድል ያደረገው የእን
ግሊዝ መንግሥት ፣ አገሪቱን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ከመሞከር
ይልቅ ለቆ ሲወጣ ፣ አሁን በ20ኛው መቶ ዓመት የዓለም ማኅበር
በቆመበትና የአፍሪካውያንና የእስያውያን ነጻነት በተቃረበበት
ዘመን ፣ በነጻነት የኖረችውን ኢትዮጵያን ለመግዛት እነ ሰር
ፊሊፕ ሚቸል ሲታገሉ መታየታቸው ነው ።

በእውነትም ጄኔራል ናፒዬር በኢትዮጵያ ቀርቼ ልግዛ ቢል
የኢትዮጵያ የ1860 ዓ. ም. ሁኔታ በብዙ ረገድ አመቺ ነበር ።
ባፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻ ያገዛዝ ዘመን (1857—60 ዓ. ም.)
የስሜን ፣ የወገራ ፣ የወልቃኢትና የጸገዴ ሕዝብ በጥርሶ ጐበዜ፣
የላስታ መካከል አማራ በዋግሹም ጐበዜ ፣ ትግራይና ትግሬ በደ
ጃች ካሣ ምርጫ ፣ ሸዋ በምኒልክ መሪነት ተከፋፍሎ ስለ ነበረ ፣
ምንም እንኳን እነዚህ ሁሉ በኋላ እንሠራርተው እንደ ችሎታ
ቸው መቃወማቸው ባይቀርም ፣ የእንግሊዝ መንግሥት በምክር



ቤት ወስኖ ባለው ጦር ላይ አዳዲስ ጨማምሮ በከፋፍለህ ግዛ
ተንኰሉ እየተጠቀመ ፣ በኢትዮጵያ ለመቆየት ቢፈልግ ለጊዜው
የሚፈነቅለው በቂ ኃይል የሚገኝ አይመስልም ።

ነገር ግን ፣ በዚህ በ19ነኛው መቶ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ
ላይ ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት ያስገደደው ፣ በቀጥታ የቅኝ አገር
ፍላጐት አለኝ በማለት ሳይሆን በዜጐቹ እስራትና በዐፄ ቴዎድ
ሮስ እምቢታ መሆኑ ጥርጥር የለውም ። ወደ ኢትዮጵያ ማሕል
ከመግባቱ በፊት ፣ እስረኞቹን ከማስለቀቅ በቀር አገር የመያዝ
ፍላጐት እንደሌለው ለሕዝቡ በገሃድ ካወጀ ወዲህ ለየመሳፍንቱ
ይኸንኑ በደብዳቤ አረጋግጦአል ። እንደገባ ተመልሶ ለመውጣ
ትም ቃሉን በተግባር ፈጽሞአል ። ይሁን እንጂ ፣ የእንግሊዝ መን
ግሥት ይህንን ፖሊሲ እንዲከተል ያደረጉትን የወቅቱን አስገ
ዳጅ ሁኔታዎች መመልከት ተገቢ ነው ።

በ19ነኛው መቶ ዓመት የእንግሊዝ መንግሥት የዘር ፣
የባህል ፣ የቋንቋ ውጥንቅጥ የመላበትን ታላቁን የሕንድ ግዛት
ከማስተዳደር ጋር ወደ ቻይናም ፣ ወደ አውስትራሊያም ያመራ
በት በአፍሪካ በተለይ በደቡብ አፍሪካ ግዛት ፣ ቦር ከሚባሉት
ከሆላንዶችና ከጀርመኖች ጋር የሚዋጋበት በጋና ፣ በናይጀሪያ
በቅኝ ገዥነት እንደ ገባ ሁሉ ወደ ውጋንዳ ፣ ወደ ኬንያ ፣ ወደ
ሴራሊዎን ለመግባት የሚያደባበት የሰዉም ፣ የገንዘቡም ኃይል
የተበታተነበት ጊዜ ነበር ።

በአውሮፓ በዊልሄም ወይም በዊሊያም ቀዳማዊና በቢስ
ማርክ የሚመራው የጀርመን መንግሥት በኃያልነት በእንግሊዝና
በፈረንሣይ ላይ በመጫኑ፣የእርሱን መስፋፋት ለማገድ በሌላ በኩል
በምሥራቅ የሩሲያ መንግሥት በባልካንና በመካከለኛው ምሥ
ራቅ ለመግባት የሚያደርገውን ጥረት ፣ ከቱርክና ከኦስትሪያ
መንግሥት ጋር ተባብሮ ለማገድ በሚደረገው ትግል በማተኮር
ላይ ስለ ነበረ ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ኃይሉን በከንቱ በታትኖ
በአውሮፓ በየግንባሩ በሚደረገው ፍልሚያ ደካማ ሆኖ መገኘ
ትን አይፈልግም ነበር ።

በዚሁም ጊዜ ፣ ከኢትዮጵያ ይልቅ የበለጠ ያተኮረው የስ
ዌዝ ቦይ በመከፈቱ የሁሉም መተላለፊያ በሆነው በግብጽ ላይ
ነበር ። በነርሱ በኩልም እየተራመደ ወደ ሱዳን ፣ ወደ መካከለኛው
ምሥራቅ ፣ ወደ በርበራ ፣ ወደ ኤደን ወደቦች ያለብዙ ጥበቃ
በዘዴና በሰላም ለመግባት የሚያደባበት ጊዜ ስለሆነ ፣ አስተዳደሩ

ውጣ ውረድ ባለበት ፣ መሳፍንቱ በውጭ መንግሥታት መገ ዛትን አጥብቀው በሚቃወሙበት በኢትዮጵያ ላይ የሰውና የገን ዘብ ኃይሉን ከማባከን ይልቅ ፣ በግብጽ ላይ ማድረግን የመረጠ ይመስላል ።

በዚህም ዘመን ፣ የቱርክ ኦቶማን ግዛት ከ16ተኛው መቶ ዓመት ዠምሮ የጦር ኃይሉ በፈቀደለት መጠን ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ በባልካን አገሮች ላይ በሰሜን አፍሪካ ያለመጠንና ያለ ምንም ቁጥጥር እየጋለበ ግዛቱን አስፋፍቶ ሳለ ፣ አሁን በ19ነኛው መቶ ዓመት ላይ ይህን ያለቅጥ የሰፋውን ግዛት በቁጥጥሩ ሥር እንደ ያዘ ለመዝለቅ የሰውም የኤኮኖሚውም ኃይል ስላልፈቀደ ለት ፣ ለመውደቅ ከመንገዳገድ ላይ እንደሚገኝ እንግሊዝ በቀጥታ ተገንዘቦታል ። በወዳጅነት ከእርሱ ጋር ሆኖ ሩሲያን ፣ አውስትሪ ያንም ስለ እርሱ ሆኖ የመቃወም መልክ እያሳየ ፣ ከእርሱ አገዛዝ በሚወጡት አገሮችና ወደቦች ላይ በዘዴ ፣ በገንዘብ ኃይልና በዝ ምድና መልክ እየገባ ለመስፋፋት ሥራዬ ብሎ የያዘበት የመን ግሥቱ መሠረታዊ ዓላማ ነበር ።

ስለዚህ ፣ በወቅቱ በነበረው ሁኔታ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛ ትነት ለመያዝ መነሣት የሚያስከትለውን መሥዋዕትነት ወጪና ችግር የእንግሊዝ መንግሥት ለመክፈል አልፈለገም ። ወይም አልተዘጋጀም ። ስለሆነም ወደ ኢትዮጵያ በቀላሉ መግባቱና በቅራኔዎችም በመጠቀም በቀላል መሥዋዕትነት ማሸነፉ ሳያ ታልለው ፣ የብዙ መኳንንት መተባበርና መለማመጥ ሳያሸን ፈው ፣ ቀርቼ ልግዛ ቢል ውሎ አድሮ የሚከተለውን መዘዝ አስቀድሞ በማመዛዘን ስተት ብሎ ወጣ ማለት ነው ።

ሁኔታውን የጀርመኑ የዚህ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትር (ቻን ስለር) ቢስማርክ ኢትዮጵያ ነጻነቷን አፍቃሪ ፣ ለማንም ቅኝ ገዥ የማትመች መሆኗን ለመግለጽ ፣ « . . . እንግሊዞች ከአቢሲ ኒያ (ሐበሻ) ለቀው ወጡ ። ለቅኝ አገር አገዛዝ የምትመች ብት ሆን ኖሮ ለቀው አይወጡም ነበር» ያለው ሁሉንም ይደመድ መዋል ። (1)

1 Le Régne De Yohannes - J. De Coursac p. 205.




# አባሪ አንድ

## ካፄ ቴዎድሮስ ደብዳቤዎች ጥቂቶቹ

ዝቲ፡ጦማር፡ዘተፈነወት፡እምኀበ፡ንጉሠ፡ነገሥት፡
ቴዎድሮስ፡ዘኢትዮጵያ፡፡
ትብጻሕ፡ኀበ፡ንግሥተ፡እንግሊዝ፡ብክቶርያ፡፡
እንዴት፡ነዎ፡ደኅና፡ነዎ፡፡
እኔ፡እግዚአብሔር፡ይመስገን፡ደኅና፡ነኝ፡፡
አቶ፡ቡላዴንጋ፡የእርስዎ፡መላክተኛ፡ነው፡ብዬ፡፡
በፍቅር፡በወዳጅነት፡ተቀብዬው፡ሰሰሁ፡፡
እስተ፡ዛሬ፡ድረስ፡ያለ መላኪ፡ባላርፍ፡ባደረጋልኝ፡ነው፡፡
አሁንም፡እርስዎም፡የክርስቶስ፡ልጅ፡ነዎ፡፡
እኔም፡የክርስቶስ፡ልጅ፡ነኝ፡፡
ስለ፡ክርስቶስ፡ፍቅር፡ወዳጅነት፡ፈልጌ ሰሰሁ፡፡
አሁንም፡ክርስቶስ፡ይሥ፡ቢለሠ ኘ ኝ፡፡
ሥንረጋ፡ዲሥታየን፡ሁሉ፡ሺ መማሊ፡ሰው፡ርኒያም ራ፡፡
ካቶ፡ቡላ ሙ ዴን፡ጋራ፡እልክ፡ሰሰሁ፡አብሮ ደስ፡እንዲለን፡፡




**ዐፄ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ**
**(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)**



በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡፡ ከአቶ፡ ብረኒ
።እንዴት፡ ሠነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስ
ገን፡ ደኅና፡ ነኝ። የምሥራች፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይ
ሏ፡ ቋፍሻ። መደ [illegible] ገገ፡ ዮሐንስን፡ የገደ
ሉን፡ ሠዎች፡ ፈጀኋቸው፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል
፡ከሚት፡ በቀር፡ ከሠልፍ፡ ያገኘሁትን፡ ሁሉ፡ ፈጀሁላ
እንድ፡ አልተውሁም። ወዲያው፡ ተከታትሎ፡ ተሸጋ
ሬ፡ ሌባ፡ ንጉሥን፡ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ ከነሠራዊ
ቱ፡ ፈጀሁት፡ አኹስም፡ ከሜዳው፡ ላይ። እንተም፡ ቶ
ሎ፡ ናልኝ። ከዕንግሊዝ፡ ንግሥት፡ ከወዳጀ፡ እግዚ
አብሔር፡ ያደረገልኝን፡ የደሥታየን፡ ወሬ፡ የምልክ
ሠው፡ የምሠድ፡ ነኝና፡ ቶሎ፡ ናልኝ፡ ይዘህልኝ፡ የም
ትሄድ፡ ነህና። የሊቀ፡ መኳስ፡ ዮሐንስን፡ የእቶ፡ ቡላዲን
ን፡ ሠዎች፡ እስታሁን፡ ያቆየኋቸው፡ ከኔ፡ ሠው፡ ካንተ፡ ጋ
ራ፡ ይሄዱ፡ ብየ፡ ነው።

**ዐፄ ቴዎድሮስ ለሚስተር ባርኒ የጻፉት ደብዳቤ**
**(እንአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)**



ዐፄ ቴዎድሮስ ለእቴጌ የተመኙ የጻፉት ደብዳቤ
(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ። ሰሚን፡እን
ዳልጥፍልህ፡እቡኑ፡ሰቃሚ፡ኮከብ፡የሚባል፡ፈላሻ። ቆንስል፡
ባላቻሁ፡የሰደዳቻሁት፡ኪምሮን። ከገዛ፡ከተማየ፡በእግዚአ
ብሔር፡ኃይል፡በፍቅር፡አስቀምጫቸው፡ሳለሁ፡ሰደቡኝ።
የእንግሊዝን፡ንግሥት፡ፍቅር፡ስፈልግ። ቡላዲን፡ዮሐንስ፡የ
ሚባሉ፡የእንግሊዝ፡ሰዎች። ከገሬ፡ቢደበደቡ። በእግዚአብ
ሔር፡ኃይል፡የነዚያን፡ደም፡ብመልስ። በዚኸውም፡ነፍሰ፡ገ
ዳይ፡ብለው፡ሰደቡኝ። ቆንሱሉ፡ኪምሮን፡የሚባለው፡የንግ
ሥት፡ሎሌ፡ነኝ፡ቢለኝ። ጃንሬን፡ጊዮ፡ሸለሚ፡ሥንቁን፡ሠ
ዋቺ፡ከንግሥት፡ወዳጅ፡አዳርገኝ፡ብየ፡ብሰደው። ከቱርኮች፡
ጋራ፡ሰንብቶ፡ተመልሶ፡መጣ። ደብዳቤየን፡ብሰው፡አልተመ
ለሰልኝም፡አለኝ። ምን፡ባደረግሁ፡ጠሉኝ፡ብየ፡በጌታዬ፡
ኃይል፡ዝም፡አልሁ።

ይድረስ፡ከሆርሙዝ፡ረሳም። አሁንም፡ትግሬ፡ሸፍታ፡ወጥ
ቶአልና። በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ዙረህ፡በመተማ፡ና፡
መተማ፡ስትደርስ፡ሳክብኝ፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ተ
ተባይ፡እሰድልሀለሁ።

ሰኔ፡በባት፡በ፳፱ቀን፡ረቡ፡ተጣፈ።

**ዐፄ ቴዎድሮስ ለሚስተር ሆርሙዝ ራሳም የጻፉት ደብዳቤ**
**(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)**

ዐፄ ቴዎድሮስ ለሚስተር ሆርሙዝ ራሳም የጻፉት ደብዳቤ
(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)

ብስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ ንጉሠ
ነገሥት፡ ቴዎድሮስ፡ ይድረስ፡ ካቶ፡ ህርሙዝ፡ ረሰም፡ እንዴ
ት፡ ሰነበትህ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስገን፡ ደህና፡ ነኝ፡
ሀኪምም፡ ብሎማንና፡ አቶ፡ ፕሪደን፡ ወንድሞችኽን፡
እንዴት፡ ሰነበታችሁ፡ አለ፡ በሉልኝ፡፡ በእግዚአብሔር
ኃይል፡ በደህና፡ ተመልሼ፡ ከቤቴ፡ ገባሁ፡ ፈረሶችን፡ ካገር
፡የነበሩትን፡ ልቀበል፡ ሂጄ፡ ነበረ፡ አሁንም፡ እግዚአብ
ሔር፡ በጤና፡ ከወዳጆቼ፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ ለመገናኘት
ያብቃኝ፡፡ ፊት፡ ስማለወዳቸው፡ አስሬ አቸው፡ ለነበር
ሁ፡ ሰዎች፡ ከናንቴ፡ እስቲገናኙልኝ፡ ድረስ፡ ከፈጣሪ
ኤችን፡ ጤና፡ ሠጥተህ፡ አድርሰልኝ፡ እያልሁ፡ እለ
ምን፡ ነበረ፡፡ ዛሬ፡ ግን፡ ከላይ፡ ለንግሥቲቱ፡ ለወደ
ጆ፡፡ ከዚህ፡ የደሥታ፡ አበባ፡ ስያዛችሁልኝ፡ ለናንተ
አጅማዊና፡ ጤና፡ ሠጥልኝ፡ እያልሁ፡ እለምናለሁ፡፡
፡እኔን፡ የሚወድበት፡ ልቡና፡ ሠጥልኝ፡ እያልሁ
እለምናለሁ፡ ፈጣሪ አቸ ኘ፡፡ እኔ ግን፡ እንግሊ
ዞችን፡ እወዳችሁም፡ እጠላችሁም፡ በዮሐንስ
ና፡ በቡላዲን፡ ጠይቃችሁ፡ እግኙት፡፡ በተቻለኝ፡
እንዳገሬ፡ እንዳቅሜ፡ ማቆሳመጤን፡ መውደዴን፡ አል
ተውሁም፡ ነበረ፡፡ እኒያን፡ መውደዴ፡ ማቆሳመጤ፡
የንግሥቲቱን፡ የናንተን፡ ፍቅር፡ አገኝ፡ ሥል፡ ነው
፡፡ አሁንም፡ ወትሮ፡ እፈልገው፡ የነበረ፡ ፍቅራችሁ፡
ተገኘልኝ፡ መስሎኝ፡ በፈጣሪአችን፡ ኃይል፡ እጅግ
ደስ፡ ብሎኛል፡፡ ታንኮኞች፡ ሠድጄላችኋለሁ፡ ካ
ለቃ፡ እንግዳ፡ ጋራ፡ ኑ፡ እንድንማከር፡ እነ ካፕቴ
ባም፡ እናንተም፡

በመጋቢት፡ በ፲፭ ቀን፡ ዓርብ፡ ተጣፈ፡፡



ዐፄ ቴዎድሮስ ለሚስተር ሆርሙዝ ራሳም የጻፉት ደብዳቤ
(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡
ንጉሠ፡ነገሥት፡ቴዎድሮስ፡ይድረስ፡ከአቶ፡ህ
ርምዝ፡ረሳም፡እንዴት፡ሰነበትህ፡እኔ፡እግዚ
አብሔር፡ይመስገን፡ደህና፡ነኝ፡፡ሀኪም፡ብ
ሉንግን፡፡አቶ፡ፕሪዶን፡፡እነአቶ፡ኪምሮንን፡እነ
አቶ፡ኮከብን፡ወንዶሞችኽን፡እንዴት፡ሰነበታ
ችሁ፡አለ፡በልልኝ፡፡እኔ፡ካንተ፡ከወዳጀ፡ጠብ፡የ
ለኝም፡ቂም፡የለኝም፡፡ቀድሞም፡መቅደላ፡የሰደ
ድሁህ፡ጊዜ፡ጠብቁ፡ብዬ፡ብልክ፡፡ፈርቶ ፡እሰ
ርነው፡ብለው፡መልሰው፡ላኩብኝ፡፡አሁንም
፡እኔን፡ወዳጅህን፡እግዚአብሔር፡ካመጣልህ፡
፡ሠንሰለቱ፡ይወጣልህ፡ተፈታ፡፡የጌቶችኽን፡
፡ሁነታ፡እስክናይ፡ድረስ፡በግዲያው፡እንጠ
ብቅሃለን፡ ፡አቶ፡ፍላጥ፡ካገርህ፡ስንቅህን፡
አምጥቶ፡ሰጥቶኝ፡ነበረ፡አገር፡ሺፍቶብ
ኝ፡ተሺካሚ፡አጥቶ፡ተበላሺብኝ፡፡ባቶ፡ፍላጥ
ባለቃ፡እንግዳ፡በ ሻለቃ፡ላይህ፡እጅ፡ሁለት
ሺ፡ብር፡ሰድጀልሃለሁ፡ተቀበል፡፡ገንዘብህ፡ስለ
ተበላሺ፡፡መቶ፡በግ፡፡አምሳ፡ፍሪዳ፡ሰድጀልሃለ
ሁ፡ተቀበል፡፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ደህና፡ሰ
መድረስ፡ቢ አበቃኝ፡ዓይን፡ሳይን፡ተያይተን፡
እንጫወታለን፡አይዞህ፡



**ዐፄ ቴዎድሮስ ለሚስተር ሆርሙዝ ራሳም የጻፉት ደብዳቤ**
**(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)**

አንተ፡ አቶ፡ ረሰአም፡ ቀጥለህ፡ ከንጉሠ ቲቱ፡ ተልኬ አለሁ
፡ብለህ፡ መጣህ፡ እኔ፡ ብዬ፡ በተቻለኝ፡ ጉልበቴ፡ በፍቅር
፡ተቀበልሁህ፡፡ የሠጠኸኝን፡ ደብዳቤ፡ ባይ፡፡ ያውሮ
ጳ፤ ሰዎች፡ ሁሉ፡ የተጣላሃቸውን፡ ያሠርሃቸውን፡
ፍታልኝ፡ ማርልኝ፡ የሚል፡ ቃል፡ አገኘሁኝ፡ እኔ
ም፡ ካንተ፡ ፊት፡ ፩ ቀን፡ ሣላሣድር፡ እኔ፡ ብዬ፡ ል
ኬ፡ እስረኞቹ፡ አስመጣሁልህ፡ በፈጣሪ አችን፡
ኀይል፡፡ ከኔ፡ ሣይደርሱ፡ አስጠምኖቹ፡ ሳንተ፡ ሰጠ
ሁህ፡፡ ወዳጅን፡ ንጉሠ ቲቱን፡ ከነመኳንንቶቹም፡
ደስ፡ ይበልም፡ ብዬ፡፡ አንተ፡ ግን፡ ምንስ፡ በድላችሁ
ነው፡ የታሠራችሁ፡ ብለህ፡ ሣትጠይቃቸው፡ በድ
ዮ፡ ተገኝቸ፡ እንደሆነ፡ ሣልክስ፡ ተበድዬ፡ ተገኝቸ፡ እን
ደሆነ፡ ከንጉሠ ቲቱ፡ ወረቀት የኀ፡ እንደገኝ፡ ሣታ
ገኝ፡ ከኔ፡ ሣታገናኝ፡ ሠደድሃቸው፡፡ ቀጥሎ
እንግሊዝ ኛ፡ ቱርክ፡ ፩ ሁነው፡ ጠሉህ፡ ብለው፡
ስማሁ፡ በዚህ፡ አዝኜ፡ ዝም፡ ብዬ፡ ተቀምጬ፡
ሣለሁ፡፡ አቶ፡ ፍላጥ፡ የደስታ፡ የፍቅር፡ ደብዳቤ፡
ላከብኝ፡፡ አሁንም፡ ሰላምህን፡ በፍቅር፡ ከኪራ
ታኝ፡ ከንጉሠ ቲቱ፡ ከመኳንንቶችም፡ ከወዳጆች
ሦ፡ ሁሉ፡ ረጪሃ፡ ወጅቂ፡ አለሁ፡ የኖበብ፡ ብል
ሃት፡ እንዲአሣዩኝ፡ በመተሃ፡ እንዲመጡል
ኝ፡ አርገህ፡ ላክ፡፡ ይህ፡ ከሆነ፡ በኋላ፡ ደስ፡ አሠ
ኝቸ፡ አሺኝቸ፡ እሰደቹኋለሁ፡ በእግዚአብሔር፡
ኀይል፡፡


ሙ፡ ሎቅ ስ፡ በወር፡ ኗ፡
ትሕሣሥ፡ በ፳፫፡ ቀን፡ ተጻ
ተጣፈ፡፡



**ዐፄ ቴዎድሮስ ለሚስተር ሆርሙዝ ራሳም የጻፉት ደብዳቤ**
**(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)**

በስመ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ፡ በሥላሴ አንድነት፡ ባንድነቱ፡ በክርስቶስ
ያመነው፡ ካሳ፡፡ መቻቻ፡ ያገሬ፡ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል እኔ ካልወረድሁ ላች
ሁ፡ ፀሐይ ቸሁን፡ አት ተዉም። ክርቲ ያኑን፡ ሁሉ፡ ጉልበት አለኝ መቅሉጣ ካረመ
ኒ፡ አገር፡ አግብቸው። ወገድ፡ የሌሳት ቀንድ፡ አለች ወገድ፡ የነበራት፡ ቀንድ፡ ነበረች
፡ ቱሳግትናም፡ የሞተባት ቀኖራስች፡ ሽማግሌ፡ ልጅ፡ የሌለው ባልቴት፡ ልጅ፡ የሌ
ሳት፡ እኔ፡ የምጠውራቸው፡ ብዙ፡ በከተማየ፡ አሉ። እግዚአብሔር፡ ከሠጣቸሁ፡ ቁ
ቀዱአቸው። ያረመኔ አገር፡ ነውና። ያገሬ፡ ሰው፡ ገብር፡ ሥራት፡ ግባ፡ ብየብለው
፡ እምቢ፡ ብሎ፡ ተጣላኝ። እየገታ፡ ግን፡ በስራት፡ በተገዛ፡ ሰው፡ አቸኔፋቹሁኝ፡ ልኔ
ን፡ ወደዉኝ፡ የተከተሉኝ፡ ሰዎች፡ እኔ፡ እርሰስ፡ ፈርተው፡ ጥለዉኝ፡ ሺ፡ ሽ፡ ብ
ተቃጡአቸው፡ ከሮጡ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ እልነበርሁም፡ ጌታነኝ መስሎኝ ባልሰላ
፡ መድፍ፡ ሠታገል፡ ውየ፡ ነው። ያገሬ፡ ሰው፡ የፈረገጅ ሃይማኖት፡ ይዞአል፡
እስልጣ እል፡ እያለ፡ እስኑግ፡ ምክን ያት፡ ይሰጠኝ፡ ነበረ። እኔ፡ ከከቱሁበት
እግዚአብሔር፡ መልካም፡ ይሠጠው፡ እኝ ይወደድ፡ ይሁን፡ እግዚአብሔር
ቢሠጠኝ ሁሉን፡ ልገዛ፡ አስብ፡ ነበረብኝ። እግዚአብሔር፡ ቢነሣኝ፡ ልሞት
አሣቢ ይዤ፡ ነበረ። ከተወለድሁኝ፡ እስታሁን፡ ወገድ፡ እጅ ን፡ ሲሰጥ፡ እያ
ውቅም ነበረ። ሰዎች፡ ሢሸሹ ተነሱቸ፡ ማራጋት፡ ልማድ፡ ረንደረኝ፡ ሲለማ
ከለከለኝ። ትሳንትና፡ በድለት፡ ያደሩቸሁ፡ ሰዎች እግዚአብሔር፡ እንደ
አይድርጋችሁ። እገኔግ፡ የሀበሻ፡ ጠላቲግ፡ ኢየሩሳሌም፡ ሄዎች፡ ቱርኮች
ን፡ እስለቅቃለሁ፡ መስሎኝ፡ ነበር። ወገድ፡ ያቀፈ፡ ወገድ፡ ተመልሶ፡ አይ
ታቀፍም።

በእሮጌ ጦርነት ፊታውራሪ ገብርዬ ከሞቱ በኋላ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ጄኔራል
ናፒዬር የጻፉት ደብዳቤ
(ከነፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት መጽሐፍ)



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንጉሠ ነገሥት

ዐፄ ቴዎድሮስ ለጄኔራል ናፒዬር የጻፉት ሁለተኛው ደብዳቤ
(ስለእስረኞቹ መለቀቅ)
(ከነፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት መጽሐፍ)

# አባሪ ሁለት

**በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት የነበሩ የመኳንንትና የሹማምንት ፥ የጸሐፊዎችና የተርጓሚዎች ዝርዝር**

ዓፄ ቴዎድሮስ ጊዜ የነበሩት መኳንንትና ሹማምንት ፣ ጸሐፊዎችና ተርጓሚዎች ስማቸው ጠፍቶ እንዳይቀር ለዝክረ ነገር ስንል ከየመጻሕ ፍቱ ለቅመን ፣ ከሰውም ጠያይቀን የቻልነውን ያህል ዝርዝራቸውን ከዚህ በታች አስፍረነዋል ። ከነዚህም ጋር ጳጳሱ አቡነ ሰላማ ፣ ዕጨጌ ወልደ ማርያም ፣ ተሰማ የሚባለውና ወጣቶቹ ልጆቻቸው ኃይሉ ካሣና ዓለማ የሁ ፣ እንደ አቤቶ ዳርጌ ማህለ ሥላሴ ፣ እንደ ባልጋዳ አርአያ ድምፁ ያሉት የየአገራቸው ትክለኛ ባላባቶች አልገቡም ። የባለቤታቸው የእቴጌ ምንትዋብ ፣ የእቴጌ ጥሩወርቅ ፣ የሚወዷቸው የወይዘሮ የተመኙ ስማ ቸው በዚያው በታሪኩ ምዕራፍ ውስጥ በያጋጣሚው ተነሥተዋልና አሁን በጽሑፍ ልናገኝ የቻልነውን የወንዶቹን የመኳንንቱን ዝርዝር ብቻ እን መልከት ።

## ያፄ ቴዎድሮስ መኳንንትና ሹማምንት ዝርዝር

| ተራ ቍ | ስምና የማዕረግ ስም | ማ መ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 1 | ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ | ያፄ ቴዎድሮስ ልጅ ከደንበኛ ሚስት ያልተ ወለዱ ፣ ከአባታቸው ፍቅር የነበራቸው አይ መስልም ፣ አስረዋቸው ነበር ። ዐፄ ቴዎድሮስ ሊሞቱ በዋዜ ማው በቃሬር በር አድርገው ወደ እንግሊዞች የገቡ ፣ ከዚያ በተከ ታዮቻቸው ታጅበው መዠመሪያ ወደ አማራ ሳይንት ፣ ከዚያ ወደ ሸዋ የመጡ የነደጃች ካሣ አባት ናቸው ። እናታቸው የሸፍ ታው ያቶ እንግዳ ወርቅ ልጅ ትሆንን ? |
| 2 | ራስ እንግዳ | የቋራ የአገው ምድር ተወላጅ ፣ ካፄ ቴዎድሮስ ጋር ከሽፍትነት ዠምሮ አብሮ አደግ ናቸው ። በፊት ቀኛዝማች እንግዳ ይባሉ ነበር ። አንባቢ እንደሚያስታውሰው ፣ በሸዋና ባብዛኛው ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመቱበት ሁሉ አብረው ዘምተዋል ። አንድ ጊዜ እስራት አግኝቷቸዋል ። በመጨረሻው ቀን ባፄ ቴዎ ድሮስ ጐን ተሰልፈው ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ራሳቸውን በገደሉ ጊዜ አብረው ተዋግተው ከወንድማቸው ከአዛዥ ፈንታ ጋር የሞቱ ናቸው ። ከመሞታቸው በፊት ጐጃምን ተሾመው ነበር ። ያያቸው ለዣን የሚባለው የፈረንሣይ ቆንሲል በጣም ቆንዦና ግርማ ያላቸው እንደሆኑ ያረጋግጣል (ገጽ 145) ማርክሃም የራስ እንግዳን አሟሟት እጠቀሰበት ላይ «አጠገቡ የነበሩትን ወጣት ልጆቹን ሕይወታቸውን ለማትረፍ ብሎ ከምሽጉ እንዲወጡ ካደ ረገ በኋላ ተዋግቶ ሞተ» ይላል ። (ገጽ 349-350) ራስ እንግዳን የውጭ አገር ጸሐፊዎች ሁሉ ላፄ ቴዎድሮስ ዋና አማካሪና እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ያደርጉዋቸዋል ። |

| ተራ ቁ | ስምና ማዕረግ ስም | ማ መ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 3 | ራስ ኪዳነ ማርያም የቀማው | የቤገምድር ተወላጅ የራስ ወልደ ማርያም ወንድም ናቸው ። ሆርሙዝ ራሳም ከራስ ዐሊ ጊዜ ዠምሮ በቤገምድር የተከበሩ ባላባት እንደ ነበሩ ፣ ባሁኑ በቴዎድሮስ ጊዜ የመቅደላ ምሽግ የበላይ ጠባቂ እንደ ነበሩ ፣ ምራላቸው ከፍ ያለ የውጭ አገር እስረኞችን የሚያጽናኑ ፣ በንጉሡ ነገሥቱ ታዘው ካልሆነ በቀር በራሳቸው ፈቃድ የሰውን ደም ማፍሰስ የማይወዱ ታላቅ ሰው ያደርጋቸውና በመጨረሻ ለሰበብ ከምኒልክ ጋር ተላልከሃል ተብለው እንደ ታሰሩ ያረጋ ግጣል ። (2ኛው ቮሊዩም ገጽ 167-168) ዶ/ር ብላንክ ምዕራፍ 13 |
| 4 | ራስ ወልደ ማርያም የቀማው | የራስ ኪዳነማርያም ወንድም ፣ ካፄ ቴዎድሮስ ሞት በኋላ ላፄ ተክለ ጊዮርጊስ አልገዛም ብለው ሸፍተው በኋላ ስለ ገቡላቸው ፣ የቤገምድር ግዛትን ሾሙዋቸው ። ተክለ ጊዮርጊስ ከደጃች በዝብዝ ጋር ተዋግተው ከሞቱ ወዲህ ፣ ላፄ ዮሐንስ አልገዛም ብለው ከንጉሥ ምኒልክም ከግብጾችም ጋር ይላላኩ ነበር ፤ በኋላም ያፄ ዮሐንስ ሹም ራስ ገብሬን ገድለው ሸፍተው ሳለ ባፄ ዮሐንስ ጦር ቤገምድር ላይ በ1867 ዓ. ም. ተገደሉ ። |
| 5 | ራስ ጸጋ (ጠጋዬ — ጠጉ) | ራሳም የራስ እንግዳ ወንድም ያደርጋቸዋል ። የጠበንዣ ያዥ ወታደር ጠቅላይ አለቃ ነበሩ ። |
| 6 | ራስ ውቤ | የዋድላ ተወላጅ ፣ ቴዎድሮስ ከዋሉበት ከብዙ የጦርነት ቦታ ውለዋል ። ራስ እንግዳ በተጋዙ ጊዜ ጐጃምን ተሾመው ነበር ። ለምኒልክ እንደ ሞግዚትም ፣ እንደ ጠባቂም ሆነው በመቅደላ መኖራቸውን አለቃ ወልደ ማርያምና አለቃ ተክሌ (ጐጃሚው) ያመለክታሉ ። (ያልታተመው ጽሑፍ ገጽ 92) |
| 7 | ራስ ገብሬ | ቤገምድሬ ፣ የስማዳ ተወላጅ ፣ ራስ ወልደ ማርያም የገደሉዋቸው ። |
| 8 | ራስ ለዳሉ | የየጁ ተወላጅ ፣ ብዙ ዘመን ከወይዘሮ ወርቂት ጋር ነበሩ ። በኋላ ለቴዎድሮስ ገብተው ፣ ዐፄ ቴዎድሮስን በወታደርነት ሲያገለግሉ ኖረው ፣ የብዙ ሰው ያላግባብ ቅጣት በተለይ 650 ዋድሎች በጥይት የተደበደቡ ጊዜ ፣ በ1859 ዓ. ም. ጦራቸውን እንደያዙ ከድተው ወደ የጁ ሸሹ ። |



| ተራ ቁ | ስምና ማዕረግ ስም | መ ማ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 9 | ራስ ባርያው ጳውሎስ | የትግሬው ተወላጅ ፣ ምኒልክ ጠፍተው ወደ ሸዋ በገቡ ጊዜ የርሳቸው ባለቤት የነበሩትን ወይዘሮ አልጣሽን አግብተው ፣ በትግሬ ለቴዎድሮስ ታማኝ ሆነው ሲኖሩ በመጨረሻ ላፄ ዮሐንስ ገቡ ። እርሳቸውም የደጃዝማች ገብረመድኅን አባት ናቸው ። |
| 10 | ራስ ባሪኮ (በርሁ) | የጐጃም ተወላጅ ፣ የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ ፣ በመቅደላው ጦርነት ከነራስ እንግዳ ጋር ሆነው ከተዋጉ በኋላ ተማረኩ ። |
| 11 | ራስ ገረሙ | ስለ እኚህ ሰውዬ እምብዛም የሚታወቅ ነገር የለም ። |
| 12 | ፊታውራሪ ገብርዬ (ገብረ ሕይወት) | ጋይንቴ ፣ ያባታቸው ስም ብላታ ጐሹ ፣ ከሽፍትነት ዠምሮ ያልተለዩ ዋና ስመ ጥር ያፄ ቴዎድሮስ የጦር አለቃ ፣ የአሮጌን ጦርነት በመምራት እዚያው ላይ የሞቱ ፣ በእንግሊዞቹ ዘንድ ሳይቀር የዠግኖች ዠግና መባልን ያተረፉ ናቸው ። |
| 13 | ካሣ (ካሥዬ) (ሳባጋዲስ) (ፊታውራሪ) | በትግሬ ያፄ ቴዎድሮስ ታማኝ በመሆን ከደጃች ንጉሤ (አገው)ም ከደጃች በዝብዝ ካሣም ተዋግተዋል ። |
| 14 | ቢተደድ ቢሠውር | ያፄ ቴዎድሮስ ያከስት ልጅ ፣ የተማሩ ማኅሌታይ ፣ ራስ ኪዳነ ማርያም ከታሰሩ በኋላ ፣ ራስ ተብለው በመቅደላ እስረኞች ላይ የተሾሙ ። አገራቸው እንፍራዝ ነው ። |
| 15 | ቢተደድ ባሕርይ | በጅርጋድ የንብረት ሹም ፣ በሰላምጌ ጦርነት የቆሰሉ ። |
| 16 | ቢተደድ ደማሽ (ደማሹ) | የጦር አለቃ ፣ የሰላምጌ ጦርነት ለት የቆሰሉ ፣ የቴዎድሮስ አብሮ አደግና ታማኝ አገልጋይ ። |
| 17 | ቢተደድ ዋ ሲ | በጭልጋ የቅማንት ተወላጅ ፣ የደጃች ቢተው አባት ፣ የፊታውራሪ ዓለማየሁ አያት (ከብላታ ገብረሕይወት የተገኙ) ። ዶክተር ብላንክ ጠባያቸውን ያመሰግናል ፤ ጉቦም በፍጹም እንደ ማይቀበሉ ያመለክታል ። |
| 18 | ፊታውራሪ በካል (በ ቃ ል) | የእልፍኝ ዘበኞች አለቃ ፣ ለቴዎድሮስ ፍጹም ታማኝ በመሆን የሰላምጌ ጦርነት ለት ሲዋጉ ግማሽ ፊታቸውን ተመትተው የሞቱ ። ማርክሃም (ገጽ 351) ራሳም ለጌታው በጣም ከመታመን በቀር እንከን የማይገኝበት ሽማግሌ ይላቸዋል ። |

| ተራ ቍ | ስምና ማዕረግ ስም | ማ መ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 19 | ፊታውራሪ ሐሰኔ (ሐሰናይ) | የመጨረሻው የመቅደላ ሹም ፣ በፊት ባሻ ሐሰኔ ወይም አሰኔ ይባሉ ነበር ። |
| 20 | ፊታውራሪ ተድላ | በመቅደላ የእስረኞች ፈረንጆች ጠባቂ ። |
| 21 | ደጃች ገለታ | በሸዋ (ጉር ሥላሴ በተደረገው ጦርነት ከን ጉሡ ወገን ሆነው ሲዋጉ የሞቱ ።) (አለቃ ዘነብ ገጽ 23) |
| 22 | ቀኛዝማች ጣዩ (ፀሐዩ) | በመቅደላ ተሾመው የነበሩ ። |
| 23 | ቢተደድ ቢሠውር | የጋይንት ተወላጅ ፣ ባሻ ቢሠውር ሲባሉ ቆይ ተው በኋላ ቢቶደድ የተባሉ ። የቢቶደድ ባሕ ርይ ምክትል የበር ዘጊዎች ሹም ። |
| 24 | ቢተደድ ኀይሉ | በጭልጋ የባላባት ተወላጅ ፣ የእስር ቤት ሹም። ጣታቸውን እጥፍ ዘርጋ በማድረግ ንግግር እንደሚያሳምሩ ማርከሃም ያረጋግጣል ። ከመቅደላው ውድቀት በፊት ወደ እንግሊዞቹ ዘወር ብለው ገብተው አገልግለዋል ። (ማርከሃም ገጽ 353-355) |
| 25 | ቢተደድ ደፋር | የጭልጋ ተወላጅ ፣ የቢቶደድ ዋሴ ምክትል ። |
| 26 | ከንቲባ ኃይሉ | የጐንደር ከተማ ከንቲባ ፣ ለእጅ ጥበበኞች ፈረንጆች ባልደረባ ። ዶ/ር ብላንክ ላዔ ቴዎድ ሮስ እንዳባት እሳዳጊያቸው እንደ ነበሩ ይገልጻል ። |
| 27 | ለፈንጉሥ ወርቁ | የደጃች መሸሻ አባት ። |
| 28 | ደጃች ዓለሚ ጓሉ | የንጉሥ አማች ፣ ከወይዘሮ (እቴጌ) የተመኙ የምትወለደዋን ያፄ ቴዎድሮስን ልጅ ያገቡ ፣ በጦርነት ሰዓት ከጸሐፊ ትእዛዝ እንግዳ ጋር በንጉሡና በእንግሊዞች መካከልመግባባት እንዲኖር የሞከሩ ። |
| 29 | ደጃች ጉጀ | የወገራ ተወላጅና የጦር አለቃ ፣ ለነራሳም እንደ ባልደረባ የነበሩ ። ራሳም ስለ ጠባያ ቸው በመጽሐፉ አመስግኗቸዋል ። (ገጽ 180) ብላንክ ባዔ ቴዎድሮስ የሚያመልኩ ሰው እንደ ነበሩ ይጠቅሳል ። |
| 30 | ደጃዝማች ባርያው | በትግሬ የራስ ባርያው ምክትል ፣ በኋላ ባዔ ዮሐንስ ዘመን ራስ ተብለው ከግብጾችም ጋር ተዋግተዋል ። የሐማሴን ገዥ በነበሩበት ጊዜ ራስ ወልደሚካኤል ገደሏቸው ። |



| ተራ ቍ | ስምና የማዕረግ ስም | ማ መ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 31 | አለቃ እንግዳ | ካለቃ ዘነብ በኋላ በመጨረሻ የነበሩ ያፄ ቴዎድሮስ ጸሐፊ ትእዛዝ ። |
| 32 | ደጃዝማች ተሰማ እንግዳ | ላጭር ጊዜ የጋይንት አገረ ገዥ ፣ ላፄ ቴዎ ድሮስ የታመኑ ዡግና መሆናቸውን ብላንክ ያወሳል ። ምዕራፍ 16 ። |
| 33 | አዛዥ ፈንታ | የራስ እንግዳ ወንድምና የሰላምጌ ጦርነት ለት ከወንድማቸው ጋር የሞቱ ። |
| 34 | ሊቀመኳስ ኪዳነማርያም | ከሊቀ መኳስ ዡን (ዮሐንስ) ቤል በኋላ ሊቀ መኳስ የነበሩ ፣ በመጨረሻ የአምባ (እስር ቤት) ሹም ሆነው ሳለ ራሳቸው በእግረ ሙቅ እንደ ታሰሩ በ1859 ዓ. ም. እንደ ሞቱ ስቴርን በገጽ 199 ይጠቅሳል ። |
| 35 | አለቃ ገብረየስ | ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ፣ ወደ ግብጽ ገዥ ተልከው የእስክንድርያውን ፓትርያርክ እየ መሩ የመጡ ፣ ባዔ ቴዎድሮስ ዘመን እንደ ታላቅ ምሁር የነበሩ ። (ሩብንሰን ገጽ 211) |
| 36 | አለቃ ዘነብ | አገራቸው ሸዋ ፣ የይፋት ተወላጅ ናቸው ። ማርቲን ፍላድ ጸሐፊ ትእዛዝ ሲላቸው ፣ ራሳም የመዝገብ ቤት ሹም ያደርጋቸውና በጠባይ በኩል ጻድ ቅና ፍጹም ክርስቲያን ይላቸዋል ። (ቮሊዩም 2 ገጽ 192-349) ብላንክ ደግሞ ፣ ኮከብ ተመራማሪ ያደርጋቸዋል ። ያፄ ቴዎድሮ ስን ታሪክና መጽሐፈ ጨዋታ መንፈሳዊ የሚባል ጽፈዋል ። ከእንግሊዞች ጋር እስከ ግብጽ ሔደው ተመልሰዋል ። መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ጋልኛና ወደ አማርኛ ከክራፍ ጋር የተረጐሙ ሲሆኑ ፣ ያረፉትም እ. ኤ. አ. በ1876 ዓ. ም. ነው ። |
| 37 | ለጋፋሪ (ደጃች መሸሻ) | ስለእኚህ ሰው እምብዛም የተጻፈ ታሪክ የለም ። |
| 38 | ደጃች ለቦዬ | ስለእኚህ ሰው እምብዛም የታወቀ ነገር የለም ። |
| 39 | ባላምባራስ ወይም ለጋፋሪ ጉላም (ገልሞ) | የቅማንት ተወላጅ ፣ በደምቢያና በቋራ ያፄ ቴዎድሮስ ምስለኔ ፣ ከሽፍትነት ዘመን ዡምሮ ከጌታቸው አልተለዩም ። የመኰንን ክንፋንና የድምባሮ ካሣን ሽፍትነት በውጊያ የደመሰሱ እሳቸው ናቸው።(አሊቃ ወልደ ማርያም፣ገጽ 29) |
| 40 | በጅሮንድ ክንፉ | የንጉሡ የንብረት ኃላፊና ባለሟል ። |

| ተራ ቍ | ስምና የማዕረግ ስም | ማ መ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 41 | መሸሻ ወርቄ | የበጅሮንድ ክንፉ ምክትል ፥ የአፈንጉሥ ወርቄ ልጅ ፥ ዶክተር ብላንክ ቀሽንት መንፋት ይወዱ እንደ ነበር ይጠቅሳል ። በኋላ ወዳፄ ምኒልክ መጥተው ባለሟል ነበሩ ። |
| 42 | ነጋድራስ ገብረ መድኅን | የንግድ ኃላፊ |
| 43 | እንግዳ ወርቀ | የሕንድ ክልስ ፥ በብዙ መልእክት ያገለገለ ያምባ ግሸን ሹም ። |
| 44 | ባላምባራስ ተሰማ | የፈረሰኞች አለቃ ። |
| 45 | ጥርሶ ኃይሉ | የንግድ ሹም ። |
| 46 | የሻለቃ ወርቄ | የበር ዘጊዎች ሹም |
| 47 | ሊቀ መኳስ ብሩ | የአምባ ግሸን ሹም የነበሩ ። |
| 48 | በጅሮንድ አደላ አዛዥ አሸቱ | ሁለቱም ከደጃች ውቤ ጋር በ1847 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት የሞቱ ፥ (አለቃ ዘነብ ገጽ 18) ። |
| 49 | አዳም ወዳጆ | መቅደላን ተሾመው የነበሩ ። |
| 50 | ይመር ጉዳና | የዋድላ ምስለኔ ፥ መንገድ አላሠራም በማለት ተገርፈው የታሰሩ ። |
| 51 | የሻለቃ ወልደ ጋብር | የዐድዋ ተወላጅ ፥ የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ ያፄ ቴዎድሮስን እሟሟት ለእንግሊዞች ያስረዱ። |
| 52 | አለቃ ፈንታ | የማኅደረ ማርያም የታወቁ ሊቅ ፥ ዐፄ ቴዎድሮስን በንግግርና በጭውውት ሲያስደስቱ ቆይተው በኋላ የተገደሉ (ወልደማርያም ገጽ 25) |
| 53 | የሻለቃ ሻተሸ | ስለእኚህ ሰው እምብዛም የሚታወቅ ነገር የለም ። |
| 54 | ባሻ መርዚን | የግሸን ሹም ። |
| 55 | መሐመድ ሠራዊ | የንጉሡ መልከተኛ (ከጐንደር ምጥዋ) በንግድ ። |
| 56 | ሻለቃ ልይህ | የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ ። |
| 57 | የሻለቃ ሊህ | የላይኛው ይሆኑ ? |
| 58 | ሊጋባ ተክሉ | በከዳተኝነት ተይዘው በጥይት የተደበደቡ ። (አለቃ ዘነብ ገጽ 42) |



| ተራ ቍ | ስምና የማዕረግ ስም | ማ መ ል ከ ቻ |
|---|---|---|
| 59 | ባሻ እንግዳ | ቴዎድሮስ የሞቱ ዕለት በውጊያው የሞቱ ። |
| 60 | አቶ ካሠኘ | የኢጋፋሪ ጉላም ምክትል ። |
| 61 | አቶ ንጉሢ | ዐፄ ቴዎድሮስ የሞቱለት በውጊያ የሞቱ ። |
| 62 | አቶ ሳሙኤል ጊዮርጊስ | ዋና አስተርጓሚ ፥ የሰናፌ ተወላጅ ፥ ለፈረንጆቹ ሁሉ እንደ ባልደረባ የነበረ ። |
| 63 | አሳላፊ ኪዳኑ | ለሸዋ ታዛቢነት ተሾሞ የነበረ ። |
| 64 | አማኒ | ያፄ ቴዎድሮስ ጋሻ ዣግሬ ፥ ቴዎድሮስ የሞቱለት ከባሻ እንግዳ ጋር አብረው የሞቱ ። |
| 65 | ልጅ አብተው | በመጨረሻ ከድቶ በበለሳ ከመዋጋቱ በፊት በንጉሡና በፈረንጆቹ መካከል ተላላኪና ባልደረባ የነበረ ። |
| 66 | ወልደ ጻድቀ መረጥ(ቀ) | የዐዲ አቦና የቋናማ ገዥ ፥ በወሰን ፍልሚያ በከሰላ አጠገብ አልገደዲ ከሚባሉ ነገዶች ጋር ሲዋጉ እንደ አው.አቆ. በ1866 ዓ. ም. የሞቱ ። (ጉስታቭ አረን ገጽ 132-3) |
| 67 | ደብተራ ደስታ | አስተርጓሚ ፥ የነራሳም ተላላኪ ። |
| 68 | ወልደ ገብርኤል | አስተርጓሚ |
| 69 | ማኅደረ ቃል | አስተርጓሚ ፥ የዐድዋ ተወላጅ ፥ በደጃች ውቤ ጊዜ ወደ ፈረንሣይ አገር ከለፌቭር ዠንድ ተልኮ ከተመለሰ ወዲህ ላፄ ቴዎድሮስም ፥ ለዐፄ ዮሐንስም ባስተርጓሚነት አገልግሏል ። |
| 70 | ሙአሊም ማታ | ካረብኛ ወደ አማርኛ ተርጓሚ ። |
| 71 | ባሻ ለምለም | ብዙ ጊዜ በመተማ ወሰን በተደረገው ውጊያ ዡብዱዋቸውን ለነሙቼ እስረኞች እየተረኩ ያጫውቱ የነበሩ ፥ አሁንም ከእንግሊዞቹ ጋር ተዋግተው የሞቱ ። (ስቴርን — ገጽ 9-10) |
| 72 | መሐመድ ሰይድ | ተላላኪ (ገሪማ ታፈረ — 243-247) |

# በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱ የመጻሕፍት ዝርዝር

## ከኢትዮጵያ


1. አለቃ ዘነብ የጻፉት የቴዎድሮስ ታሪክ ፣ ኢኖ ሊትማን ያሳተሙት
፪. አለቃ ወልደ-ማርያም የጻፉት የዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ፣ ሞንዶን ቪዳዬ ያሳተሙት
3. ስሙ ባልታወቀ የተጻፈ የዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ሉዊጂ ፉዚላ ያሳተሙት
4. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ከጸሐፊ ትዕዛዝ ገ/ሥላሴ
5. ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ከነጋድራስ አፈ-ወርቅ ዘብሔረ ዘጌ
6. መይሳው ካሣ ፣ የቋራው አንበሳ ፣ ከገሪማ ታፈረ
7. አንድ ለናቱ ፣ ከአቤ ጉበኛ
8. የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ
9. የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ
10. ታሪክ ነገሥት ፣ ፓሪስ በቁጥር 342 የተቀመጠ
11. ዋዜማ ፣ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
12. ያፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ፣ ከኰንዘልማን
13. የሕይወት ታሪክ ፣ ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
14. መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፣ ከመንግሥቱ ለማ
15. የግራኝ አህመድ ወረራ ፣ ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ
16. ያልተጠረዘ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጽሑፍ
17. ያልታተመ የራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ያጤ ቴዎድሮስ ታሪክ
18 የልታተመ የለቃ ተክለ ሥላሴ የእጅ ጽሑፍ

# ከውጪ አገር ጸሐፊዎች


**Abbadie** (frnaud d')
— Douz Ans de Séjour dansl a Haute - Ethiopia (Abyssinie) Tome I, Paris, *1968*.

**Acton** (Roger)
— The Abyssinian Expedition, London, *1816*

**Blanc** (Henry)
— A Narrative of Capitivity in Abyssinia . . . London, *1868*.

**Bruce** (James)
— Travels to Discover the Source of the Nile . . . Edenburgh, *1790*.

**Budge** (Wallis)
— A History of Ethiopia (Nubia and Abyssinia) London, *1928*.

**Conti-Rossini** (Carlo)
— La Cronaca reale abyssina, Roma, *1917*.
— Historia Regis Sertse Dengel, Paris, *1907*.
— Vicende del Etiopia e delle Missione Catoliche al tempi di Ras Ali, Roma, *1916*.

**Coulbaux** (J.B.)
— Vers la Lumiére, Paris, *1926*.
— Historique Politique et Religieuse de l'Abyssinie . . . , Paris, *1926*.

**Coursac** (J. De)
— Le Règne de Yohannes, Rome, *1926*.

**Dei Sabelli** (Luca)
— Storia di Abyssinia, Roma, *1936—38*.

**Delboca** (Angelo)
— Gli Italiani in Africa Orientale, Roma, *1925*.

**David Appleyard and Richard Pankhurest**
- The Last Two Letters of Emperor Tewodros II of Ethiopa (April II and 12 1868)

**Fusela** (L.)
— La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia, Univ. Orientale de Napoli, *1954—6*.

**Girma Selassie Asfaw and David L. Appleyard**
— In Collaboration with Edward Ullendorff Oxford 1979.
— ORIENTAL DOCUMENTS II
— The Amharique Letters of Emperor Theodore of Ethiopia to Queen Victoria and her special envoy.

**Guidi** (I.)
- Annales Regum Iyassu II et Iyoas, Paris, *1912*.
- Annales Johannes, Iyassu I, Bekaffa, Paris, *1903*.

**Holland and Hozier**
- Record of the Expedition to Abyssinia, London, *1870*.

**Hozier** (Henry)
- The British Exepadition to Abyssinia, London, *1925*.

**Littman** (E.)
- The Chronicle of King Theodore of Abyssinia, Princeton, *1902*.

**Markham** (C.R.)
- A History of the Abyssinian Expedition, London, *1969*.

**Massaioc** (G)
- I miei trentacinque anni di Missione nell' alta Etiopia, Romma, *1921*.

**Monroe** (E.) **and Jones** (A.H.M.)
- Histoire de l'Abyssinie, Paris, *1935*.

**Moorhead** (A.)
- The Blue Nile, N.Y., *1910*.

**Mosley** (L.)
- Il Negus (Traduzione de Letitzia Berrini), Milano, *1968*.

**Napier**
- Field Marshall Napier of Macdala—A Memoire by his son, Bombay, *1868*.

**Pankhurest** (R.)
- The Emperor Theodore and the Question of Foreign Artisans in Ethiopia, Boston, *1966*.

**Rassam** (H.)
- Narrative of the Mission . . ., Vol. II, London, *1860*.

**Rosenfield** (p.)
- A Chronology of Menelik II, Michigan State Univ., *1976*.

**Rubenson** (S.)
- The Survival of Ethiopian Independence, A.A.U.P., *1976*.
- Correspondance and Treaties *1800—1854*, North—Western Univ.P., *1987*.

**Stern** (H.)
- The Captive Missionary . . ., London, *1868*.

**Vidaillet** (M.)
- Chronique de Theodros II, Paris, *1905*.